# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 221 ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!















ፎቶ - ዳኜ አበራ

# “ኢትዮጵያ መከራና ችግሯን መጋራትን መሰረት ባደረጉ ሁለት መንገዶች ማለፍ ትችላለች”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ መከራና ችግሯን መጋራትን መሰረት ባደረገ ሁለት መንገዶች ማለፍ ትችላለች ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ 200 የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ትናንትና የማዕድ ማጋራት ስነስርዓት አድርገዋል። በወቅቱም ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢትዮጵያ የውልደት ስብራቷን፤ መከራዋንና ችግሯን በሁለት የመጋራት መንገዶች ማለፍ ትችላለች ሲሉ ተናግረዋል።

አንደኛው መንገድ እንደባህላችን፣ እንዳደግንበትና እንደልማዳችን መሰረት ችግርን በመካፈል መከራውን ማለፍ ይጠይቃል። ብዙዎች ችግርና መከራውን ከሌሎች ጋር በመካፈል ችግሩ ጥቂቶችን ተጭኖ እንዳይጎዳ ያግዛሉ። ይህ ልምዳችን ችግርን በመካፈል መከራውን

“ኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ መልካሙ ሹምዬ

## የአምነስቲና የሂዩማንራይትስዎች ጥምር የምርመራ ሪፖርት አድሏዊና ችግር ያለበት መሆኑን ኢሰመኮ ገለጸ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስዎች ያወጡት ጥምር የምርመራ ሪፖርት የመረጃ አሰባሰብ፣ የመረጃ ትንተና፣ ድምዳሜውና በመፍትሄነት ያስቀመጡት ሃሳብ አድሏዊና ችግር ያለበት መሆኑን ኢብን (የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ) ገለጸ፡፡

የአምነስቲና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ‹‹በወልቃይት ጠገዴ ያልተነገረ ካልሆነ በስተቀር ያልተፈጸመ የግፍ አይነት የለም››

-ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ

ወርቁ ማሩ

ሁመራ፡- አሸባሪው ሕወሓት በኢትዮጵያ በተለይም በወልቃይት፣ ጠገዴና ሁመራ ሕዝብ ላይ ሳይነገር የቆየ ካልሆነ በስተቀር የግፍና የጭካኔ አይነቶችን ሁሉ መፈፀሙን የወልቃይት ጠገዴና ሁመራ አካባቢ ጊዜያዊ ምክትል አስተዳዳሪና የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ ተናገሩ፡፡ ቡድኑ አንዱን ከፍ፤ ሌላውን ዝቅ በማድረግ የቅኝ ገዢዎችን የአገዛዝ ስርዓት ሲከተል እንደነበርም ተናግረዋል፡፡

ኮሎኔል ደመቀ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለምልልስ እንደገለፁት፣ ቡድኑ የውጭ ወራሪዎችን ተልዕኮና ማኒፌስቶ ይዞ ሲሰራ የመጣ ኃይል በመሆኑ ስልጣን ከያዘ በኋላ ህዝቡን በዘር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት እና

“በወልቃይት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ








## ሕብረተሰቡ መጪዎቹን በዓላት ሲያከብር አደጋ እንዳያጋጥም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት

- የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

ገጽ 4







# ''በተልተሌ ወረዳ የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ቶሎ መፍትሄ ካልተበጀለት አስጊ ነው ''

- ተልተሌ ወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት

# ''የተከሰተው የአንበጣ መንጋ አስጊ ደረጃ ላይ አይደለም''

- ግብርና ሚኒስቴር

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፦ በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ተልተሌ ወረዳ የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ከወዲሁ መከላከል ካልተቻለ በሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል የተልተሌ ወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ።ግብርና ሚኒስቴር በበኩሉ የተከሰተው የአንበጣ መንጋ እንደባለፈው የሚያሰጋ አይደለም ሲል ምልሽ ሰጥቷል ።

ተልተሌ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አማረ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘንድሮ የአንበጣ መንጋ ወረራ ለሁለተኛ ጊዜ በወረዳው ተከስቷል። የመጀመሪያው የአንበጣ መንጋ ከሕዳር እስከ መጋቢት 28 ቀን 2014ዓ.ም ድረስ ተከስቶ የተለያዩ ጉዳቶችን አስከትሏል። ከወረዳ እስከ ፌዴራል መንግሥት ድረስ በቅንጅት በተደረገው የመከላከል ሥራም 19 መንጋ ማጥፋት ተችሏል።ቀሪው የአንበጣ መንጋም ወደ ደቡብ ኦሞ ዞን ሀመር አካባቢ ሸሽቷል ።

ሁለተኛ ዙር የአንበጣ መንጋ ወረራም ከሚያዝያ 7ቀን 2014ዓ.ም ጀምሮ በተደጋጋሚ እየተከሰተ እንደሚገኝ አመልክተው፤ የተከሰተው የአንበጣ መንጋም ለመራባት የደረሰ፣ መብረርና መብላት የሚችል በቁጥር አምስት መንጋ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአንበጣ መንጋው እንዳይስፋፋም በየደረጃው ለሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ቶሎ መፍትሔ እንዲሰጡ ማሳወቃቸውን ገልጸዋል።

ግብርና ሚኒስቴር ቀድሞ በቦታው በመገኘት የአንበጣ



መንጋ መከሰቱን ማረጋገጡን ጠቁመው፤መንጋውን ለማጥፋም በአይሮፕላን የታገዘ የኬሚካል ርጭት መካሄድ እንደሚኖርበት ተገንዝቦ በየቀኑ ክስተቱን እንደሚከታተሉ ገልጸውላቸው መመለሳቸውን ነግረውናል።

ተልተሌ ግብርና ጽህፈት ቤት የተቻለውን ያክል በጂፒኤስ (GPS) በመታገዝ የአንበጣ መንጋውን እንቅስቃሴ በመከታተል ሪፖርት እያቀረቡ እንገኛለን ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ እስካሁን የአንበጣ መንጋውን ለማጥፋት በአይሮፕላን የታገዘ የኬሚካል ርጭት አለመጀመሩን ተናግረዋል።

ጽህፈት ቤቱ አንበጣ መጋውን መከላከል የሚያስችለው እስከ 50 ሜትር ርቀት ኬሚካል የሚረጭ መሳሪያ ከግብርና ሚኒስቴር በድጋፍ ማግኘቱን ገልጸው፤ መንገድ በሌለባቸው ረግረጋማ አካባቢዎች መድረስ አስቸጋሪ መሆኑን አብራርተዋል።

አንድ የአንበጣ መንጋ 400 ሄክታር መሬት ማውደም እንደሚችል ገልጸው፤ እስከ አሁን ድረስ በተደረገው መከላከል አንድ ጊዜ ብቻ በ30 ሄክታር መሬት ላይ በሚገኝ አንበጣ መንጋ ላይ የኬሚካል ርጭት በማካሄድ ማጥፋት ተችሏል ብለዋል።

እንደ አቶ ብርሃኑ ገለጻ፤ በወረዳው በሚገኙ 12 ቀበሌዎች አራት ሺህ 238 ሄክታር የእርሻ መሬት፣ ሰባት ሺህ 672 ሄክታር የግጦሽ መሬት ፣ስምንት ሺህ 471 ሄክታር የደን መሬትና አምስት ሺህ የ762 አባወራ መሬት ይዞታ ላይ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል። እስከ አሁን ድረስ ሶስት የአንበጣ መንጋ የት እንደደረሰ ባይታወቅም ወረዳው ድንበር አካባቢ ከመሆኑ አንጻር ወደ ኬንያ ሊሄድ ይችላል።

ወቅቱ በልግ እንደመሆኑ ከወዲሁ መፍትሔ ካልተበጀለት ወደፊት በሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል ያሉት ኃላፊው፤ ኦሮሚያ ክልል መንግሥት በስልክ ጉዳን ከመከታተል በዘለለ በአካል አልተገኘም ብለዋል።

ኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ምክትልና እጸዋት ጥበቃ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደጀኔ ሕርጳ በበኩላቸው፤ቢሮው ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሰው ጀርባና በመኪና ላይ ሆነው የሚረጩ ኬሚካሎችንና ቁሳቁሶችን ለወረዳው ግብርና ጽህፈት ቤት ድጋፍ አድርጓል። አሁን ባለው ሁኔታ የአንበጣ መንጋውን መቆጣጠር አለመቻሉን ጠቅሰዋል።

ቢሮው ችግሩን ከወዲሁ በፍጥነት ለመፍታትም ከግብርና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር የአይሮፕላን ኪራይ ውል በመፈራረም ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል ።

በአይሮፕላን የታገዘ የኬሚካል ርጭት እስኪካሄድ ድረስም ሕብረተሰቡና ባለሙያዎች ችግሩን ለመቅረፍ የበኩላቸውን አስተዋጽዎ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የዕጽዋት ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ በላይነህ ንጉሴ በቦረና ዞን ተልተሌ ወረዳ በቅርቡ የተከሰተውን የአንበጣ መንጋ ለመከላከል ኬሚካል የሚረጩ መኪናዎችና ባለሙያዎችን ወደ ስፍራው በመላክ በመከታተል ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

የአንበጣ መንጋው በአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ላይ ያደረሰው ጉዳት እንደሌለ ተናግረዋል ። የሚታየው ስጋት ባለፈው በአንበጣ መንጋ የተከሰተውን አደጋ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ጠቁመው፤አሁን የተከሰተው የአንበጣ መንጋ በአካባቢው በዝናብ እጥረት ስላለ የአንበጣ መንጋው መራባት በማይችልበት ደረጃ በመሆኑ የሚያሰጋ አይደለም ብለዋል።

የአንበጣ መንጋው ከተከሰተ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተደረገው ክትትልም አብዛኛው የአንበጣ መንጋ የሰፈረው በደን ውስጥ በመሆኑ በአይሮፕላን የታገዘ ኬሚካል ርጭት ማጥፋት እንደሚቻል ጠቁመው፤ ይህም በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚጀመር ገልጸዋል።

# የምገባ ማዕከላት ማህበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን እያስቻሉ መሆኑ ተጠቆመ

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- የምገባ ማዕከላቱ ለነዋሪው አቅም ከመፍጠር፣ የማህበራዊ ትስስር ከማጠናከር እና ማህበራዊ ፍትህን የማስፈን ሚናቸውን እየተወጡ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ገለጸ። የምገባ ማዕከላቱን በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑ ተጠቁሟል።

የኤጀንሲው ኃላፊ ወይዘሮ አንቺነሽ ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የምገባ ማዕከላቱ ለነዋሪው አቅም በመፍጠር፣ የማህበራዊ ትስስርን ከማጠናከር እንዲሁም ማህበራዊ ፍትህን ከማስፈን አንጻር ሚናቸውን እየተወጡ ነው።

ትግበራው የተጀመረው በከተማዋ በቀን አንድ ጊዜ የራሳቸውን ምግብ መሸፈን የማይችሉ ዜጎች በመኖራቸው ነው። ማዕከላቱም በቀን የዕለት ጉርስ የሌላቸው ዜጎች ጉርሳቸውን አግኝተው እንዲውሉ የማስቻል ዓላማን ይዘው የተገነቡ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በዚህ መሠረት በቀን አስር ሺህና ከዚያ በላይ የሆኑ ዜጎችን በማዕከላቱ እየተመገቡ ነው።ይህም ለነዋሪው አቅም ከመፍጠር፣ የማህበራዊ ትስስር ከማጠናከር እንዲሁም ማህበራዊ ፍትህን ከማስፈን አንጻር ትልቅ ሚና እንዳለው አመላክተዋል።

“ያለው ያመጣል የሌለው መጥቶ ይመገባል” በሚል እሳቤ መንግሥት ማህበራዊ ፍትህን በከተማዋ ለማስፈን ሚናውን እየተወጣ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በማዕከላቱ ጥራትን ያስጠበቀ ዘለቄታዊነት ያለው አገልግሎት መስጠት አንዱ ሥራ ሲሆን፤ ከዚህ ጎን ለጎን የማስፋፋት ሥራዎችም ይከናወናሉ። በዚህም ተደራሽ ያልሆኑ አካባቢዎች ላይ ማዕከላቱን የማስፋፋት ሥራ ይሰራል። ኤጀንሲው በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጡ ካሉት ማዕከላት በተጨማሪ በመዲናዋ ባሉት ሁሉም ክፍለ ከተሞች የምገባ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እቅድ ይዞ እየሰራ ሲሆን፤ የማስፋፊያ ሥራውን በተመለከተ ጥናት ተጠንቶ ኤጀንሲው ከለጋሾች ጋር በመነጋገር ላይ ይገኛል።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ የምገባ አገልግሎቱን እስካሁን ስድስት ክፍለ ከተሞች ላይ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። አገልግሎቱን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች ቢያንስ አንድ ማዕከል ተደራሽ ለማድረግና በቀሪዎች አምስት ክፍለ ከተሞች ላይ ቀሪ ሥራችን ለማከናወን እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። በተለይ በጉለሌና ኮልፌ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራም ጠቅሰዋል።

ማዕከላቱን ለማስፋፋት እቅዶች ቢኖርም፤ በቅድሚያ አሁን ላይ ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ማዕከላት ዘለቄታዊ የሆነ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ጥራትን ማዕከል ያደረገ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም ወይዘሮ አንቺነሽ ገልጸዋል። “የጥራት ሥራውን ከማከናወን ጎን ለጎን የት አካባቢዎች ላይ ተጨማሪ ማዕከላት መከፈት አለባቸው የሚለው ጥናት ተሰርቶ ከለጋሾች ጋር እያወራን ነው ያለነው። በዚህ መሠረት ማእከላቱ የሚስፋፉ ይሆናል” ብለዋል።

ማዕከላቱን ከማስፋት በፊት የተከፈቱ ማዕከላትን ጥራት መሥራት ቀዳሚው ሥራ እንደሆነ አንስተው፤ ይህም ያለውን አገልግሎት ማሻሻል፣ ቋሚ ማድረግ፣ ተጠቃሚዎችን መልሶ መለየትና መሰል ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን እንደሚያካትት ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት ያለው አጠቃላይ የምገባ ማዕከላቱ ቁጥር ስድስት ሲሆኑ፤ በቀን ከአስር ሺህ በላይ ሰው እንደሚመገቡ ከኤጀንሲው የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

# በአገሪቱ ከፍተኛ የደም እጥረት ማጋጠሙን ብሔራዊ ደም ባንክ አስታወቀ

## -ያለው የመጠባበቂያ ደም ክምችት ከአምሥት ቀናት የማይበልጥ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በመላ አገሪቱ ከፍተኛ የደም እጥረት መከሰቱንና ያለውም የመጠባበቂያ ደም ክምችት ከአምሥት ቀናት የማይዘል መሆኑን ብሔራዊ ደም ባንክ አስታወቀ።

በብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት የደም ለጋሾች ዘርፍ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶክተር ተመሥገን አበጀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በአገሪቱ ያሉት የሁለቱ ትላልቅ ሃይማኖቶች ተከታዮች ፆም ላይ መሆናቸውን ተከትሎ በመላ አገሪቱ ከፍተኛ የደም እጥረት ተከስቷል።በአገሪቱ ያለውም የመጠባበቂያ ደም ክምችት ከአምሥት ቀናት የማይበልጥ ነው።

በአገር ደረጃ ሲታይ ከፆም በፊት በዚህ ዓመት የነበረው የደም ክምችት አመርቂ የሆነበት ዓመት ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የዐቢይ እና ረመዷን አፁዋማት ከገቡ በኋላ የመደበኛ ደም ለጋሾችም ሆነ ሌሎች ለጋሾች ቁጥር ማሽቆልቆሉን ተናግረዋል።

ይህም የደም ክምችት ላይ ከፍተኛ እጥረት እንደፈጠረ አመልክተው፤ በተለይ እንደ ፕላትሌት የደም ተዋፅዖ እና ‘ኦ’ የደም ዓይነት ክምችቶች እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ብለዋል።

ፕላትሌት የሚባለው የደም ተዋፅዖ ለካንሰር ታማሚዎችና የደም መፍሰስ ችግር ላለባቸው ታካሚዎች የሚሰጥ የደም ዓይነት መሆኑንና ያለው ክምችት ለአንድ ቀን ብቻ ሲሆን ‘ዖ’ የተባለው የደም ዓይነትም በዛ ቢባል ለሁለት ቀናት የሚሆን ክምችት መኖሩን አመልክተዋል።

በአዲስ አበባ ያለውን የደም ፍላጎት እንደ አብነት ወስደው ያስረዱት ዶክተር ተመሥገን ፕላትሌት የሚባለው የደም ተዋፅዖ ብቻ ከ200 ዩኒት በላይ በቀን እንደሚያስፈልግ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የሌሎች የደም ዓይነቶች በአሁኑ ጊዜ ያለውም የደም ክምችት መጠን ዝቅተኛና ለአምሥት ቀናት መጠባበቂያ እንደሆነና ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ሊሆን የሚችል እንደሆነ በአፅንዖት ገልፀዋል።

ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ብቻ ከ350 እስከ 400 ዩኒት ደም በየቀኑ ይሰበሰብ እንደነበር አስታውሰው፤ የተለዩ ደም የመሰብሰብ መርሐ ግብሮች ሲኖሩ ደግሞ እስከ አንድ ሺህ



ዶክተር ተመሥገን አበጀ

ዩኒት እና ከዚያ በላይ መሰብሰብ ይቻል ነበር፤ አሁን የለጋሾች ቁጥር ከግማሽ በታች መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአገሪቱ ያሉ የመደበኛ ደም ለጋሾች ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑ ለክምችቱ መቀነስ ተጨማሪ ምክንያት መሆኑን ገልጸው፤ እንደ አገር ሲታይ ከአጠቃላይ የደም ለጋሾች ቁጥር መደበኛ የደም ለጋሾች ቁጥር ከ5 እስከ 8 በመቶ ብቻ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የአዳዲስ ደም ለጋሽ ቁጥር የመጨመር አዝማሚያ በየጊዜው ቢታይም የመደበኛ ደም ለጋሾች ቁጥር ግን መሻሻል እንዳላሰየ አመልክተው፤

ካሁን በፊት በተናጠል፣ በቡድን እና በተቋማት ሲደረግ የነበረውን የደም ልገሳ ፕሮግራሞች ተጠናክሮ እንዲቀጥል ዶክተር ተመሥገን ጥሪያአቸውን አስተላልፈዋል።

በፆም ወቅት በተገቢው መጠን ደምን ሊተካ የሚችል ፈሳሽ በመውሰድ መለገስ እንደሚቻልና ምንም ዓይነት ጉዳት እንደሌለው ዶክተር ተመሥገን ገልፀዋል።

በሰሞነ ሕማማት እና አፁዋማት ላይ ያለው ማኅበረሰብ ደም በመለገስ በዓሉን ቢያከብረው ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል ብለዋል።

ደም ባንኮች በማንኛውም ሰዓት ክፍት ስለሆኑ ደም ለጋሾች በፈለጉት ሰዓት ሄደው ደም መስጠት እንደሚችሉና አሁን በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ እየተከበረ ያለውን ሰሞነ ሕማማትን ደም በመለገስ ለበጎ ነገር ተጠቀሙበት ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

መጪዎቹን በዓላት ስናከብር በሞትና በሕይወት መካከል ሆነው የእኛን ደም የሚፈልጉትን ሳንረሳ ይሁንም ብለዋል።



# ‹‹አገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን በሂደቱ ሳይ መተማመን ፈጥሮ መስራት ይገባል››

-ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ
የታሪክ ተመራማሪ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የተጀመረው አካታች የሆነ አገራዊ መግባባት ግብ እንዲመታ በሂደቱ ላይ መተማመን ፈጥሮ መስራት እንደሚገባ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ ገለጹ።

ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አካታች አገራዊ ምክክር መደረጉ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በምክክሩ የታሰበው ውጤት እንዲገኝ በሂደቱ ችግርም ሊያጋጥም እንደሚችል በመገንዘብ ለችግሩ መፍትሔ መፈለግ ይገባል። ውጤቱ ከሚያመጣው ጥቅም ይልቅ ያልታሰቡ አደጋዎችን ይዞ እንዳይመጣ በቂ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ማድረግም ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ሹመት ገለጻ፤ አገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ወገኖች ማሳተፍ የሚችል መሆን አለበት። አካታች የሆነው አገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆንና የተፈለገው አገራዊ መግባባት ላይ እንዲደረስ በሂደቱ ላይ ምን መተማመን አለ?፤ ሂደቱ በሰዎች እይታ ምን አይነት ቅቡልነት አለው? የሚለውን ግምት ውስጥ አስገብቶ መስራት ቁልፍ ጉዳይ መሆን አለበት ብለዋል።

በአገራዊ ምክክሩ ሂደት ከተሳታፊዎቹ መካከል ሂደቱ በሰመረ መንገድ እንዳይካሄድ ከራሳቸው ጥቅም ጋር ላይጣጣም ይችላል። ለአብነት አንዳንድ ቡድኖች ጥቅማችን የሚረጋገጠው በአመጽ እንጂ በሰላማዊ ሂደት አይደለም ብለው የሚያስቡ ቡድኖች ከመጀመሪያው ጀምሮ በእንቢታና ኮሚሽኑን በመክሰስ ስለሚጀምሩ ይሄን መሰል ችግርና አደጋ እንዳለ ግምት ውስጥ ያስገባ ሥራ መስራት ያስፈልጋል።

አካታች አገራዊ ምክክር ለማካሄድ በሚደረገው ሂደት አጋፋሪ የሆነው መንግሥት ለምክክሩ ያለው እይታና በሕዝብ ያለውን ቅቡልነት ማጤን ይገባል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ በሕዝብና መንግሥት መካከል ያለውን አመኔታ ማሳደግ በአገራዊ ምክክሩ ሂደት ላይም መተማመን እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል።

የአገራዊ ምክክሩ ሂደት ሰላምን በማስፈንና የህዝብን ደህንነት በመጠበቅ፣ ህግ በማስከበር፣ ሁኔታዎች ከእጅ እንዳይወጡ ይቆጣጠራል የሚል አመኔታ በሕዝቡ ዘንድ መኖር መቻል አለበት። ይህ እምነት መኖር ሲችል ሕዝቡ በጎ ጫና በመፍጠር አገራዊ ምክክሩን ብዙ ኃይሎች እንዲቀበሉትና እንዲሳካ ማድረግ ያስችላል።

እምቢተኞችን ማሳመን የሚችለው ሕዝብ ነው። አፈንጋጭ የሆኑ ኃይሎችን ከአገራዊ ምክክር ማፈንገጥ እንዳይችሉ የማድረግ አቅም ያለው ሕዝብ ነው። ሕዝቡ ደግሞ በመንግሥት እምነት ካጣ በሂደቱ ላይ ጫና የማሳደር አቅሙ ይዳከማል። ስለሆነም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለው አመኔታ ሊጠናከር ይገባል ብለዋል።

ተቀናቃኝ የሆኑ ፓርቲዎች በራሳቸው ጉዳይ አገራዊ ምክክር ሂደቱን ሊያጣጥሉት ቢችሉም የሚያቀርቡትን ቅሬታ መንግሥት በማዳመጥ ትክክለኛ ሆኖ ሲገኝ በመርህ ላይ የተመሰረተ ማስተካከያ ሊያደርግ ይገባል። በተጨማሪም ከፓርቲ መዋቅር ውጭ ያለው ሕዝብ አስተያየትና ስሜት በአግባቡ በማዳመጥ ውጤታማ አገራዊ ምክክር ሊደረግ ይገባል ብለዋል።

# “መሬት ነክ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት ገንዘብ እየተጠየቅን ነው”

- የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች

**ሞገስ ተስፋ**



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ለሕዝብ እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች ምን መልክ አላቸው የሚለውን ለመመልከት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ በአዲስ አበባ ከተማ በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ተገኝቶ ምልከታ አድርጓል። በዚህም አገልግሎት ለማግኘት ነዋሪዎች ከሌሊቱ አሥራ አንድ ሰዓት ከቤታቸው ተነስተው ተራ ለመያዝ ክፍለ ከተማው በር መገኘታቸውን ነግረውታል።

የሥራ ሰዓት ደርሶ ሁሉም አገልግሎት ለማግኘት በየፊናው ይራወጣል። ይሁንና በክፍለ ከተማው ውስጥ አገልግሎት ፈላጊዎች እንዴትና የት አገልግሎት ማግኘት እንዳለባቸው መረጃ የሚሰጥ አካል የለም። በተለያዩ ጉዳዮች አገልግሎት ለማግኘት በር ላይ ቆመው የሚጠባበቁ ሰዎች እርስ በርሳቸው አገልግሎት ለማግኘት አሰልች እና አድካሚ መሆኑን ያወራሉ።

ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ አቶ በላይ አበራ (ስማቸው የተቀየረ) የተባሉ አዛውንት እንደነገሩን ፋይላቸው ከየካ ክፍለ ከተማ ወደ ለሚኩራ ክፍለ ከተማ ተዘዋውሮ የገዙት ቤት የካርታ ሥራው በየካ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት አልቆ ቤዚክ ማፕ ተረጋግጦ ሊሰጠኝ ሲል ፋይልህ ወደ ለሚ ኩራ ክፍለከተማ ስለተዛወረ እዚያ እንዲሄዱ ይነገራቸዋል። በተነገራቸው መረጃ መሰረት ወደ ለሚኩራ ክፍለ ከተማው ቢሄዱም አገልግሎት ማግኘት ግን አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ገልጸዋል።

መሬት ነክ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት እንዲህ በቀላሉ አትስተናገድም የሚሉት ተገልጋዩ፣ ፋይል ለመፈለግ የእጅ መንሻ የሚሆን ከሁለት ሺ እስከ 40 ሺ ብር ጉቦ የምንጠየቅበት ሁኔታም አለ ይላሉ።

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት እግዱ ከተነሳ በኋላ ባለፈው የካቲት ወር የጀመሩትን የቤት ስም ማዛወር አገልግሎት ሥራው ያለቀ ሆኖ እያለ አገልግሎቱን ሲጠይቁ አንዴ ካርታ የለም፤ ካርታ ሲመጣ ደግሞ ፋይሉ አልተለየም የሚሉ ሰበቦችን እያበዙ አገልግሎት ማግኘት መቸገራቸውን በምሬት ይገልጻሉ።

ችግሩ በክፍለ ከተማው ብቻ የተወሰነ አይደለም የሚሉት አገልግሎት ፈላጊው አዛውንት፤ ወረዳዎች ላይ ባሉት የመሬት አስተዳደሮች ጭምር የሚታይ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡ በተለይም ወረዳ 14 ከፍተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር መኖሩንና የተወሰኑት ሰራተኞቹ በቀን እስከ 60 ሺ ብር ከአገልግሎት ፈላጊው በሙስና መልክ ገንዘብ እንደሚሰበስቡ መስማታቸውን ገልጸዋል።

ሌላኛዋ ቅሬታቸውን ያካፈሉን ወይዘሮ ዘውዲቱ አበባው (ስማቸው የተቀየረ) ተገልጋይ ለሁለት ወራት ያህል አገልግሎት ማግኘት እንዳልቻሉ ገልጸው፤ ለፎርማ፣ ፋይል ለማውጣት፣ ማህተም ለማስረገጥ ቀጠሮ ያበዛሉ። በክፍለ ከተማው ውስጥ በተለይም በመሬት ልማት ማኔጅመንት ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ግልጽነት የጎደለውና ማህበረሰቡን ያማረረ ነው። የበላይ አመራሩ እንዴት ችግሩን መፍታት እንዳልቻለም ጥያቄ እየፈጠረብን ነው ሲሉ ምሬታቸውን ገልጸዋል።

በግልጽ የፋይል መፈለጊያ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠየቅበት ሆኗል። ተገልጋዩን የሚመጥን የሰው ኃይል አለመኖሩም ለሙስና በር ከፍቷል ሲሉም ተናግረዋል።

ወይዘሮ አስካለ ጋዲሴ (ስማቸው የተቀየረ) እንደሚሉትም ቤት ገዝተው ስም ለማዘዋወር አንድ ወር ከ15 ቀን ቢመላለሱም አገልግሎቱን ማግኘት አልቻሉም። የሕዝብ ፋይል በዘፈቀደ ሜዳ ላይ ተበትኖ ያለበት ብቸኛው ክፍለ ከተማ ለሚ ኩራ ስለመሆኑም ይናገራሉ።

የተበተነውን ፋይል ቅዳሜና እሁድ በዘመቻ ገብተውና አደራጅተው በማስቀመጥ የሚስተዋለውን አሰልች የፋይል ፍለጋ በመቅረፍ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። ነገር ግን ፋይል ለመፈለግ ጉቦ መቀበል እየተለመደ ስለመጣ ይህን ማድረግ አይፈልጉም ብለዋል።

ስሜን ለደህንነቴ እና አገልግሎቱን ለማግኘት ስል መናገር አልፈልገም ያሉት ሌላኛው አገልግሎት ፈላጊ ክፍለ ከተማው ውስጥ አገልግሎት ለማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነው። የመጣሁት የንብረት ስም ዝውውር ለማግኘት ነው። ይህን አገልግሎት ለማግኘት ለበርካታ ወራት ብመላለስም በአገልግሎቱ አሰጣጡ የተንዛዛና የተወሳሰበ በመሆኑም ምክንያት ጉዳዩን እስካሁን ማጠናቀቅ አልቻልኩም ሲሉ ተናግረዋል።

ስለሆነም በመመላለስና በቀጠሮ ብዛት እየተንገላታሁ ነው። በተለይ አገልግሎት ለማግኘት የሚመጣውን የክፍለ ከተማው ማህበረሰብ ስርዓት ባለው መንገድ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያደርግ ሁኔታ የለም፤ ይህም እኔን ጨምሮ ሁሉንም አገልግሎት ፈላጊዎች እያማረረን ነው ሲሉ ነግረውናል።

በክፍለ ከተማ ውስጥ ከአንድ አገልግሎት ክፍል መረጃ ጠይቆ አገልግሎቱ በትክክል የሚሰጠው በየትኛ ክፍል እንደሆነ መረጃ የሚሰጥ አካል የለም። በዚህም ሳቢያ ህብረተሰቡ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል ሲመላለስ ጊዜውን አባክኖ ምንም አገልግሎት ሳያገኝ ወደ ቤቱ የሚመለስበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡

የነዋሪዎችን ቅሬታ በቦታው ተገኝቶ የተመለከተው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የክፍለ ከተማውን የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ኃላፊ በጉዳዩ ላይ ምላሽ እንዲሰጡ በአካል ጥያቄ ቢያቀርብም ተገልጋይን እያስተናገድኩ ስለሆነ በስልክ ምላሽ እሰጣለሁ በማለት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥተው ነበር።

ይሁንና ቀጠሮ በሰጡን ቀን በተደጋጋሚ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ብንደውልላቸውም ስልካቸው ስለማይነሳ ምላሻቸውን ማካተት አልተቻለም። ጉዳዩን አስመልክቶ ምላሽ ለመስጠት ከፈለጉ ግን ሀሳባቸውን የምናስተናግድ ይሆናል።

# በጦርነት ውስጥ ሆነው የማለፊያ ነጥብ ያሳመጡ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ድጋሚ እንዲፈተኑ ተወሰነ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-በጦርነትና ግጭት ውስጥ ሆነው የተፈተኑና የማለፊያ ነጥብ ያላመጡ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከ2014 ዓ.ም መደበኛ ተፈታኞች ጋር እንዲፈተኑ ውሳኔ ተላለፈ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር ከክልል እና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ጋር ተከታታይ ውይይት በማድረግ የተለያዩ ውሳኔዎችን በትናንትናው እለት አሳልፏል።

በመግለጫው የ2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ፈተና እርማት በተመለከተ ያጋጠመ ችግር አለመኖሩን ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

በአብዛኞቹ ክልሎች ያጋጠመ የውጤት መቀነስ መኖሩን እና ትምህርት ሚኒስቴር አማራጮችን የማየት ሥራ መሥራቱንም በመግለጫው ተነስቷል።

በዚህም በጦርነትና ግጭት ውስጥ ሆነው የተፈተኑ አካባቢዎች እና የማለፊያ ነጥብ ያላመጡና ወደ መንግሥት ዩኒቨርሲቲ መግባት ያልቻሉ ተማሪዎች በ2014ዓ.ም በሚሰጠው የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና እንደ መደበኛ ተማሪ እንዲፈተኑ ውሳኔ ተላልፏል።

ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ውይይት በማድረግ ተጨማሪ የቅበላ አቅም እንዲኖር ከስምምነት ላይ መደረሱን እና ተጨማሪ የቅበላ አቅም በፍትሃዊነት በጦርነቱ ምክንያት ለተጎዱ ክልሎች እንዲከፋፈል ውሳኔ ተላልፏል።

የፈተና ውጤት ማሳወቅን በተመለከተም በሁለት ዙር ፈተና በመሰጠቱ አጋጥሞ የነበረው ችግር መታረሙ በመግለጫው ተገልጿል።

በመጀመሪያው ዙር ተፈታኞች በስነ-ዜጋ ትምህርት ካጋጠመው ችግር ውጪ ሌሎች ችግሮች ባለማጋጠማቸው የሌሎች ትምህርት ዓይነቶችን ውጤት ውድቅ ለማድረግ አሳማኝ የውጤት ትንተና አለመኖሩም ነው የተገለጸው።

በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ቅበላ የሚያገኙትን በተመለከተ በቀደምት ዓመታት ከመሰናዶ ትምህርት በኋላ ከሚፈተኑ ጋር በማነጻጸር የተፈጠረ አለመረዳት መኖሩንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

በቀጣይም እንደዚህ አይነት ችግሮች እንዳይፈጠሩ የተጠናከረ ሥራ ለመሥራት ከስምምነት ላይ መደረሱ ተገልጿል።



ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

# ሕብረተሰቡ መጪዎቹን በዓላት ሲያከብር አደጋ እንዳያጋጥም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት

## - የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

አዲስ አበባ፡- ሕብረተሰቡ መጪዎቹን የፋሲካና የኢድ-አልፊጥር በዓላት ሲያከብር የእሳት አደጋ እንዳያጋጥም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና ድንገተኛ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አሳሰበ።

ሕብረተሰቡ መጪውን የፋሲካና የኢድ-አልፊጥር በዓላትን ሲያከብር የአደጋ ስጋቶችን ከመነሻቸው በመለየት አስቀድሞ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርበት ኮሚሽኑ ዛሬ በሰጠው መግለጫ አስታውቋል።

የመዲናው የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽነር አቶ ሶሎሞን ፍስሃ እንደገለፁት፣ ሕብረተሰቡ ከበዓላቱ አከባበር ጋር ተያይዞ የአደጋ ስጋቶችን ሲመለከትና አደጋ ሲያጋጥም በ939 ነጻ የስልክ መስመር በመደወል ፈጣን አገልግሎት መጠየቅ ይኖርበታል።

ለዚህም ተቋሙ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ከሕዝቡ በሚደርሰው ጥቆማ መሠረት ምላሽ ለመስጠት በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ባለፉት 9 ወራት ባጋጠሙ የእሳት አደጋዎች ምክንያት የ104 ሰዎች ሕይወት ማለፉንና 154 ሰዎች ደግሞ ቀላልና ከባድ የመቁሰል አደጋ እንዳጋጠማቸው ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

በዚሁ ጊዜ በአዲስ አበባና አካባቢው በአጠቃላይ 377 አደጋዎች ማጋጠማቸውን አብራርተዋል።

ከእነዚህ ውስጥ 251 የሚሆኑት የእሳት ቃጠሎ አደጋዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 126 አደጋዎች ከእሳት ውጪ ያሉ ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች መሆናቸውን በመግለጫው ላይ ተካቶ መቅረቡን ከአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።



አቶ ሶሎሞን ፍስሃ

## "ኢትዮጵያ መከራና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የምናሳልፍበት መንገድ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዐቢይ ገለጻ፤ ሁለተኛ መንገድ ደግሞ ትግሉን መካፈል ነው። ችግሩን ከስሩ ነቅሎ ለመጣል የሚያስችለው መንገድ እራሱ ትግሉን መካፈል ነው። በዚህ አግባብ ችግሩን ለማለፍ የሚደረገውን ትግል መካፈልም ወሳኝነት አለው።

ያለንን የማናካፍል ፤ ችግሩን ለመቅረፍ ደግሞ ትግሉን የማንካፈል ከሆነ ግን መከራ የዘለቀባትና በችግር የተሞላች አገር ይዘን መቀጠላችን አይቀርም ብለዋል።

ይህን ለመቅረፍ ደግሞ በአጭር ጊዜ አካሄድ ችግሮቻችንን የምንካፈል መሆን ይገባል። በረጅም ጊዜ ልምዳችን ደግሞ በጋራ ራዕይ በሕብረትና በአንድነት ችግሮቻችንን በመታገል ጥረት ማድረግ አለብን። በዚህም ልጆቻችን ይህን አይነት መከራ እንዳያገኛቸው ማድረግ ይኖርብናል ሲሉ ተናግረዋል። እነዚህ ሁለቱ መከራን የመጋራትና ትግሉን የመካፈል መንገዶች ለአገራችን በጣም አስፈላጊ ጉዳዮች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ያለንን ማካፈልና ማዕድ ማጋራት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የኖረ ዕሴታችን ነው። ሁሉም በያቅሙ ያለው ለሌለው እያካፈለ ነው እዚህ የደረስነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ማዕድ ስናጋራም አዲስ የባህል ልምምድ ሳይሆን የዘለቅንበት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማወቅ ያለብን ማካፈል ለራስ ነው፤ መስጠትም ለራስ ነው ። ሰው የዘራውን ነው የሚያጭደው። ባካፈልነው ልክ ዛሬ ባናየውም ነገ በልጆቻችን ላይ እናየዋለን ሲሉ ተናግረዋል።

ከልምዳችንም ማየት እንደሚቻለውም በኀዘን ቤት እንኳን ኀዘንተኛው የስሜት ስብራቱ የከፋ እንዳይሆን በመተሳሰብና በመደጋገፍ ውስጥ ኀዘኑ ቀለል እንዲለው ጎረቤቱ ሁሉ ያለውን አካፍሎ ያጽናናዋል። በገጠርም ሰው ውሃ ጠምቶት ቢጠይቅና ምግብ አሊያም ወተት ቢሰጠው ክፈል አይባልም፤ ይህ የማዕድ ማጋራት ልምዳችንን ይበልጥ ማሳደግ አለብን ብለዋል። ዛሬ የተቸገረም እንዲሁ ነገ መርዳትና ሕይወት መታደግ ይችላል። ይህን አምነን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለን ላይ ጥቂት እያካፈለ ብዙዎችን ማጽናናት ይጠበቅበታል ሲሉ አሳስበዋል።

ተደጋግፈን ብዙዎችን ማዕድ ብናጋራና ዕንባቸውን ብናብስ መጪዎቹ የፋሲካና የኢድ በዓላትን እጅግ ያማረ ማድረግ ይቻላል። በተለይ በፋሲካ እና በኢድ በዓላት ወቅት በእጅጉ የተለመደውን ማዕድ የማጋራት ባህላችንን አጠናክረን መቀጠል እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

በዚህ በጎ ምግባር ብዙዎች በደስታ የሚያሳልፉባቸውን ቀናት መፍጠር የምንችልበት ዕድልም አለን። መልካምነት ጊዜ ጠብቆ ስለሚከፍል ሁላችንን ካለን ላይ ተካፍለን በዓላቱን ሰላምና በፍቅር ልናሳልፍ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ባደረጉት የማዕድ ማጋራት ስነስርዓት የተለያዩ የምግብ ግብዓቶችና ለጓሮ አትክልት አዘገጃጀት ማሳያ የሚሆን በፕላስቲክ ዕቃ የተተከለ ችግኝ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ 200 ሰዎች ተበርክቷል።

## የአምነስቲና የሂዩማንራይት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የአብን ምክትል ሊቀመንበር አቶ መልካሙ ሹምዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተቋማቱ ያወጡት ሪፖርት ዓለም አቀፍ የምርመራ ደረጃን አያሟላም፤ አድሏዊና ችግር ያለበትም ነው።

የተዛባና የአንድ ወገን ፍላጎትን ለማሳካት የተሰራ፣ ሕወሓት በኃይልና በጠመንጃ አፈሙዝ ሞክሮ ያላሳካውን በዲፕሎማሲና ዓለምአቀፍ ጫና ፈጥሮ ለማሳካት ታቅዶ የተተገበረ ፖለቲካዊ ዓላማን ለማሳካት የተሰራ ሪፖርት መሆኑንም አመልክተዋል።

በተለይም በሰብዓዊ መብት ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ከተባለ ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ መረጋገጥ ይኖርበታል። ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን በስልክ በማነጋገር ተሰርቷል ያሉትም ቢሆን ተገቢውን የመረጃ አሰባሰብ ደረጃን አያሟላም ብለዋል።

ለሰብዓዊ መብት መከበርና መጠበቅ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እንደግፋለን። ደረጃቸውን የጠበቁና ገለልተኛ ምርመራዎችም እንዲካሄዱ እንፈልጋለን። እነዚህ ተቋማት ግን የምዕራባውያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሆነው የሚያገለግሉ በመሆናቸው አካሄዱን እናወግዛለን።

መግለጫው ከሰብዓዊ መብት ሪፖርትነት ይልቅ የፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሃሳብነት የሚጎላ ነው። የአማራ ሕዝብ ባለፉት 30 ዓመታት ተደጋጋሚና መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥቃት ተፈጽሞበታል። ምዕራባውያን በጦርነቱ ወቅት ይዘውት የነበረው አቋም ከሞላ ጎደል ሕወሓት ይዟቸው የነበሩ ሃሰተኛ ክሶችን እንደእውነት ተቀብሎ በማስተጋባት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ላይ ጫና ለመፍጠር ሚሞከሩ ነበር። በአጠቃላይ ተቋማቱ የሕወሓት አላማ ማስፈጸሚያ አካል ሆነው ተገኝተዋል።

ሪፖርቱ በየትኛውም መስፈርት የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም፣ ደረጃውንም አያሟላም። ሃሰተኛ መረጃን በመጠቀም ምዕራባውያንና ዓለም አቀፍ ተቋማትን ያሳምንልናል ያሉትን ሃሳቦችን በመጠቀም ማሰራጨታቸው ትክክል አለመሆኑንም አመልክተዋል።

በሪፖርቱ ወልቃይት፣ ጠገዴንና ሁመራን በሌላ ስያሜ ደምድሞ መጥራቱ ትክክል አይደለም። ይህ አካባቢ በታሪክና በነበረው መጠሪያ የሚታወቅ ነው፤ ወልቃይት ጠገዴና ሁመራ ጠቅለል ተደርጎ የሚጠራው ወልቃይት ተብሎ ነው።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ «ምዕራብ ትግራይ» ላለፉት 30 ዓመታት ትህነግ የሰየመው ስያሜ ነው። ገለልተኛ ለመባል ቦታውንም በተመለከተ የእከሌ አንልም ቢሉም በተጨባጭ መነሳቱ ተገቢ አይደለም። ሪፖርቱ አድሏዊና ሃሰተኛ መረጃን መሰረት ያደረገ ነው።

ሕወሓት አብዛኛውን ጊዜ ሃሰተኛ መረጃዎችን በማሰራጨት ይታወቃል። በተለያየ መንገድ በርካታ ዜናችን አስፍሯል፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከምዕራብ ትግራይ እንደተፈናቀሉ ጭምር የሃሰት መረጃ ሲያሰራጭ ነበር። ይህንን ተቀብለው የሪፖርቱ አካል ማድረጋቸውንም ጠቁመዋል።

የቤቶችና ሕዝብ ቆጠራ የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ባለስልጣን ሥራ ነው። የቆጠራ ዳታዎቹንና ግምታዊ ስሌቱን አስቀምጧል፡ ሆኖም በቀድሞ ማንነቱ ሙሉ በሙሉ በሕወሓት የበላይነትና ፍላጎት መመራቱን አስታውሰዋል።

ዳታዎቹን ሲያስቀምጡ የራሳቸውን ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ መሆኑ ይታወቃል። የማዕከላዊ እስታትስቲክስ የዞኑ ነዋሪ ብሎ ያስቀመጠው መረጃ 410 ሺህ 662፣ የተባበሩት መንግሥታትም በተመሳሳይ 467 ሺህ 890 ነው።

ይህ ሕዝብ ትህነግ ማንነቱን የካደው፣ በጉልበት ትግሬ ነህ ብሎ የሰየመው የአካባቢው ማህበረሰብ ግን ራሱን አማራ ነኝ ብሎ የሚጠራ፣ በአማራነቱ የሚያምንና ሲታገል የኖረ የአማራ ሕዝብ ነው።

መረጃው ተገኘ የሚለውም ወደ ሱዳን ከሄዱት በተለይም ማይካድራና ሁመራ አካባቢ የነበሩ ጭፍጨፋዎችን የፈጸሙ የትህነግ ሚሊሻዎችና ወደ ምስራቅ ሱዳን ከተሻገሩት የሳምሪ ቡድን አባላት ነው። እነዚህ ሰዎች በአማራ ሕዝብ ላይ የዘር ጭፍጨፋ የፈጸሙና በህግ የሚፈለጉ ሰዎች ናቸው።

የተቋማቱ ሪፖርት ተጠቂውን አጥቂ በተቃራኒው ደግሞ አጥቂውን ተጠቂ አድርጎ ያስቀመጠ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ሪፖርቱ በአማራ በኩል ያለውን መፈናቀልና ግድያ አለማንሳቱ አድሏዊነቱን በግልጽ እንደሚያሳይም ጠቁመዋል።

በተለይም የወልቃይት ማንነት እንቅስቃሴዎችን ሲመሩ የነበሩ ሰዎችን በወንጀለኛነት ሲከሰስ በአንጻሩ የዘር ጭፍጨፋን የመሩ የሕወሓት ሰዎችን አንዳቸውንም በግለሰብ ደረጃ በስም ጠቅሶ ተጠያቂ አለማድረጉንም ጠቁመዋል።

## ‹‹በወልቃይት ጠገዴ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በአካባቢ እየከፋፈለ እርስ በእርሱ እንዲባላ ሲሰራ የኖረና አሁንም ያንኑ ካላስቀጠልኩ እያለ የሚዋጋ ኃይል ነው።

ሕወሓት ኢትዮጵያን ለማጥፋት በቅድሚያ አማራን ማጥፋት ነው የሚል ትርክት በመያዝም በተለይ በአማራ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ግፍና መከራ መፈጸሙንም ተናግረዋል።

ይህ ቡድን በይፋ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦል ድረስም ቢሆን እንሄዳለን ያለ ኃይል ነው ያሉት ኮሎኔል ደመቀ፤ ይህ ደግሞ ትልቁ የጥፋት ኃይል መሆኑን ምስክር እንደሆነ ጠቁመዋል።

ሕወሓት የኢትዮጵያ ዋነኛ ጠላት የሆኑት የውጭ ኃይሎች ታዛዥና ጉዳይ አስፈጻሚ በመሆኑም በዚህ ኃይል ነጮቹም ሲጠቀሙ ኖረዋል፣እየተጠቀሙም ናቸው ብለዋል ኮሎኔል ደመቀ፤ አሁንም በኢትዮጵያ ላይ እያደረጉ ያለው ተጽዕኖ እና ጫና ይህን ለማስቀጠል ያለመ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የወልቃይት ሕዝብ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ከሕወሓት ጋር ሲዋጋ ነበር ያሉት ኮሎኔል ደመቀ፤ በወቅቱ በተለይ ታሪክ የሚያውቁ ትላልቅ የወልቃይት ሰዎችን በግፍ እንደጨፈጨፈና በወልቃይት ጠገዴ ቀዝቃዛ የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈፀሙንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተገኙት የጅምላ መቃብሮች ምስክር መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

በመሆኑም ሕወሓት ባለፉት አርባ ዓመታት የፈፀማቸውን የዘር ማጥፋት ወንጀሎች የዓለም ማህበረሰብ እና ሚዲያዎች በስፍራው በመገኘት ሊያዩት እና እውነታውን ሊረዱ ይገባል ብለዋል።

ኮሎኔል ደመቀ እንዳሉት፣ ባለፉት አርባ ዓመታት በርካታ የወልቃይት ሕዝብ ከቤቱ እንደወጣ ቀርቷል፤ ብዙዎቹ በእስር ቤት ተጉላልተዋል፤ ሌሎች ደግሞ ከፍተኛ ስቃይና መከራ ተቀብለዋል። የብዙዎቹ አስከሬንም የት እንደተቀበረ እንኳን አይታወቅም።

እንደ ኮሎኔል ደመቀ ገለጻ፤ ሕወሓት ማንም በማይገምተው ሁኔታ በአየር ማረፊያ ጭምር ሰዎችን በድብቅ በማገትና በጅምላ በመጨፍጨፍ ከፍተኛ ኢሰብዓዊ እና ዘግናኝ ተግባር ሲፈጽም ነበር። በዚህም በሁመራ አየር ማረፊያ ብቻ ከ90 በላይ የጅምላ መቃብር ተገኝቷል።

ሕወሓት በወልቃይት ማህበረሰብ ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ በመፈፀም እና አብዛኛውም እንዲሰደድ በማድረግ በምትኩ ቀደም ሲል ከደርግ ጋር ሲዋጉ የነበሩ የትግራይ ተወላጆችን አስፍሯል ያሉት ኮለኔል ደመቀ፤ የአካባቢውን የስነ ሕዝብ አሰፋፈር ስርዓት ለመለወጥም ስም እስከመቀየር ደርሷልም ብለዋል።

በወልቃይት የተፈፀመው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ በከፍተኛ ተንኮልና በስውር የተፈፀመ በመሆኑ አብዛኛው ህዝብ ወጥቶ ከመቅረት ውጭ እንዴት እንደተገደለ፤ የት እንደተቀበረ እና መቼ እንደሞተ እንደማይታወቅም ጠቁመዋል። በዚህ የተነሳ እስካሁን ድረስ በርካታ ሰዎች ልጆቻቸው፤ አልያም የተለያዩ የቤተሰብ አባላት የት እንደገቡ ሳያውቁና እርማቸውንም ሳያወጡ እንደሚገኙ ነው የተናገሩት።

በሌላ በኩል የወልቃይት ሕዝብ የማንነት ጥያቄዎችን ሲያነሳ መኖሩን የጠቆሙት ኮሎኔል ደመቀ፤ ለዚህ ጥያቄ ግን ምላሹ መገደልና መሰደድ ሆኖ ኖሯል ብለዋል። በመሆኑም አሁንም መንግሥት ለጥያቄያቸው ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ ጠይቀዋል።

በተለይ የህልውና ዘመቻውን ተከትሎ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ከአሸባሪው ሕወሓት ነጻ ቢወጣም እስካሁን ድረስ በመንግሥት በጀት የማይመደብለት በመሆኑና በአካባቢውም ያለው መሰረተ ልማት በአሸባሪው ሕወሓት በመውደሙ በአሁኑ ወቅት ህብረተሰቡ በችግር ላይ ይገኛል ብለዋል።

በተለይ የመብራት አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ በመቋረጡ የህክምና አገልግሎትና ሌሎች የልማት ሥራዎች በከፍተኛ ሁኔታ መስተጓጎላቸውንና በዚህም ከፍተኛ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳቶች እየደረሱ መሆኑን ኮሎኔል ደመቀ ተናግረዋል።

የውጭ ኃይሎችም ለሽብር ቡድኑ ድጋፍ እንዲደረግ እየጮሁ፤ ላለፉት አርባ ዓመታት መከራ የደረሰበትን የወልቃይት፣ ጠገዴና ሁመራ ሕዝብ ዝም ማለታቸው ተገቢ አለመሆኑን ኮሎኔል ደመቀ ተናግረዋል።

ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ የወልቃይት ጠገዴ አማራ የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ጉዳያቸውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለማቅረብ በ2007 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በሄዱበት ወቅት በወቅቱ በሕወሓት ከፍተኛ አመራሮች ተይዘው ከፍተኛ እንግልት የደረሰባቸው ሲሆን በ2008 ዓ.ም ደግሞ በጎንደር ከመኖሪያ ቤታቸው አፍነው ሊወስዷቸው ከመጡ የወያኔ የጸጥታ ኃይሎች ጋር በመፋለም ከፍተኛ ትግል ማድረጋቸው ይታወሳል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ ይፋ ባደረገው ጥናት እንዳመለከተው በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት አካባቢዎች ሕወሓት በፈጸመው ግፍና መከራ የተነሳ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ 26 ነጥብ 5 ከመቶ ለስደት ተዳርጓል፤ 19 ነጥብ 5 ከመቶ ታፍኖ የት እንደገባ አይታወቅም፣ እንዲሁም 29 ከመቶው ደግሞ ለሞት ተዳርጓል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የወታደራዊ መረጃ ተቋማቱ ትብብር በችግር ለሚታመሰው ምስራቅ አፍሪካ ትልቅ ጥቅም አለው!

የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ካለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እስትራቴጂ የብዙ ኃያላን አገራት ትኩረት ከመሆን አልፎ፤ ሁሉም እጁን ሊያስገባበትና የራሱን ጥቅም ማስጠበቂያ ይሆነኛል ያለውን ወታደራዊ መሰረት ሳይቀር ለመገንባት እሽቅድምድም ውስጥ የገባበት አካባቢ ሆኗል። ይህ ሁነት ደግሞ በሃያላኑ መካከል ከሚፈጥረው ሽኩቻ በዘለለ ቀጣናው የተረጋጋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አውድ እንዳይኖረውና በሰላምና ጸጥታ ችግር እንዲታመስ አድርጎታል።

ይሄን ችግር ከመፍታት አኳያ እነዚህ ኃያላን ነን የሚሉ አገራት የየራሳቸውን ስትራቴጂ ይዘው ከመቅረብና እግረ መንገዳቸውን የራሳቸውን ጥቅም የማስጠበቅ ግባቸውን ከማሳካት የዘለለ ጠብ የሚል ውጤት ሳይመጣ ዛሬም ቀጣናው ብቅ ጥቅል በሚል የግጭት አውድ፣ አልፎም የጦርነት ቀጣና ሆኖ ለመገለጽ በቅቷል። ይሄ የሰላምና ፀጥታ ችግር ደግሞ ቀጣናው የጠነከረ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዳይኖረው፤ ይልቁንም በተደጋገመ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ለድርቅ፣ ረሃብ፣ መፈናቀልና ለበሽታ ተጋላጭነቱን ከፍ አድርጎታል።

የሰላም እጦት፣ ድርቅ፣ ረሃብና ሌሎችም አሉታዊ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና መገለጫ ሊሆኑ ግድ ያላቸውን ችግሮች ከማስወገድ አኳያ ታዲያ፤ "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" እንዲሉ፤ በቀጣናው የሚስተዋሉ ችግሮች ምንም እንኳን በራሱ በቀጣናው የተፈጠሩም ባይሆኑ፤ ችግሩ በቀጣናው ላይ የተንሰራፋ እንደመሆኑ ችግሩን ከመፍታት አንጻርም ቀጣናዊ መፍትሄ ሊሰጠው ግድ ይላል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም፣ ማህበራዊ መስተጋብርና የኢኮኖሚ ትስስርን ማጎልበትን ታሳቢ ያደረገ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂ በመንደፍ ወደ ሥራ መግባቷ ይታወቃል።

ይሄን የኢትዮጵያ አቅጣጫ የሚደግፉ ዘርፈ ብዙ ቀጣናዊ ሥራዎች ሲከናወኑም ቆይተዋል። ለአብነትም በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ፣ በሶማሊያ፣ በጂቡቲ፣ በኬንያና ሌሎችም የኢትዮጵያ አጎራባች አገራት መካከል የነበረን ችግር ከመፍታትና የተሻለ ግንኙነትና ትብብር እንዲፈጥሩ በማድረግ ረገድ ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ሚና ተወጥታለች። በስራዎቹም ውጤት ማምጣት ተችሏል። ይሄ በመሆኑም ቀጣናው ቀድሞ ከሚታወቅበት የሰላምና ጸጥታ ሥጋት መጠነኛ መሻሻሎች ታይተውበታል። ችግሮች ሲያጋጥሙም ተናብቦና ተጋግዞ ችግሮችን አሸንፎ የማለፍ አካሄድ ተስተውሏል።

ከሰሞኑም የዚሁ ጅማሮ አጋዥ የሚሆን የምስራቅ አፍሪካ ወታደራዊ የመረጃ ተቋማት ሽብርተኝነትን ለመከላከልና የቀጣናውን ዘላቂ ሰላም የማስጠበቅ ትብብርን በስምምነት ፊርማ እውን ማድረጋቸው ተሰምቷል። ይህ ስምምነት የተፈጸመው የምስራቅ አፍሪካ የመከላከያ ወታደራዊ መረጃ መድረክ በኢትዮጵያ አዘጋጅነት በአዲስ አበባ በተካሄደበት ወቅት ሲሆን፤ በጋራ ለመስራት የተደረሰው ስምምነትም ምሥራቅ አፍሪካ የምትታወቅባቸውን የጸጥታና ደህንነት ሁኔታ ሽብርን፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እንዲሁም ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር አይነት ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የጸጥታና የደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል የቀጣናው አገራት በትብብር ለመሥራት የሚያስችላቸው መሆኑ ነው የተነገረው።

ከዚህ በተጨማሪም ይሄን አይነት ስምምነት በዘመነ ግሎባላይዜሽን አንድ አካባቢ ያለው መልካም አጋጣሚም ሆነ ስጋት በአንድ አካባቢ ብቻ የሚወሰን ባለመሆኑም፤ በአገር ውስጥ ለሚፈጠሩ ችግሮች (ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ አሸባሪዎቹ ሕወሓት እና ሸኔ የፈጠሩትን አይነት የሽብር ተግባርና የሕዝቡ ደህንነት አደጋ ላይ በመጣል ያደረሱትን በደል አይነት ችግሮች) ከመከላከል አኳያ ለአገራቱ የተሻለ የመረጃ መለዋወጫ አውድ በመፍጠር ችግሮቹን ለመከላከል ዕድል የሚፈጥርም ይሆናል። ለዚህ እውን መሆን ግን የምስራቅ አፍሪካ አገራት ሽብርተኝነትን ለመከላከል ትብብርን ማዕከል ያደረገ ሥራ መሥራት ስለሚጠበቅባቸው፤ በተለይ እንደ ጅቡቲ ካሉ የተለያዩ ኃያላን አገራት የጦር ቤዝ መቀመጫ ከሆነች አገር ጋር በወታደራዊ የመረጃ ልውውጥ ደረጃ ቀጣናዊ ትብብር መፍጠርና በጋራ መስራት ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ፣ አካባቢያዊ ዘላቂ ሰላምን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስርንና የጋራ ብልጽግናን ለማምጣት የሚያስችል መሪ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች። በተለይም ለጎረቤት አገራት ትኩረት በመስጠት በአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች መካከል ሁሉን አቀፍ ትብብርና ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የሕዝብ ለሕዝብ ፎረም መመስረት፣ የድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ሃብቶችን ጨምሮ ከውጭ ግንኙነታችን ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ጉዳዮችን በሚመለከት በዕውቀትና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ተቋማዊ አቅም መገንባትን ግቧ አድርጋ እየተንቀሳቀሰች ይገኛል።

ኢትዮጵያን ጨምሮ ጁቡቲ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ታንዛንያና፣ ኡጋንዳ በተሳተፉበት መድረክ የተደረገው ይህ ስምምነት፤ በመሰረታዊነት የምስራቅ አፍሪካ ወታደራዊ መረጃ ተቋማት በድንበር፣ በሳይበር፣ በማህበራዊ ሚዲያ ዙሪያ፣ በማህበራዊ ጉዳዮች፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በወጣቶችና ሥራ አጥነት በሌሎችም ጉዳዮች በጋራ መሥራትን ታላሚ ያደረገ ነው። ይህ ይበል የሚያሰኝ የቀጣናውን መሰረታዊ ችግሮች ለማቃለል ትልቁን ሚና የሚጫወት የትብብር ሰነድ እውን የሆነበት ነው። ይሁን እንጂ የቀጣናው ችግር በመከላከያው መስክ በሚደረግ ትብብርና አብሮ የመስራት ሂደት ብቻ መቋጫ የሚያገኝ አይሆንም፤ ይልቁንም በፖለቲካዊው፣ በማህበራዊው፣ በኢኮኖሚያዊውና ዲፕሎማሲው መስክ የበለጠ አብሮና ተቀራርቦ በመስራት ሊደገፍና ሊታገዝ፤ ኢትዮጵያ በቀጣናው እውን ለማድረግ እንደጀመረችውም የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራዎች፤ የመሰረተ ልማትና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶች እንዲጠነክር ማስቻል ያስፈልጋል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

## ሃይ ባይ ያጣው የጫኝና አውራጆች ሕገ-ወጥነት

ሜሳት ኢያሱ

የሰው ልጅ ለሶስቱ ሕጎች እየተገዛ ሊኖር ግድ ይለዋል። ለሕገ-ልቦና፣ ለሕገ-እግዚአብሔር /ፈጣሪ/ እና ለሕገ-መንግሥት። ለሕገ-ልቦና/ለሕሊና ተገዢ መሆን ተፈጥሯዊ ጸጋ ነው። ሰው መጥፎ ነገር ከማድረግ ይልቅ ጥሩ ነገር በመሥራት ለህሊና ዳኝነት የሚገዛበትና የሞራል ልዕልናውን ከፍ የሚያደርግበት ውስጣዊ እሳቤ ነው። አባቶቻችን ‹‹ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፤ ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም››የሚሉትም ለዚህ ነው።

ሕገ-እግዚአብሔር/ፈጣሪ የምንለው ደግሞ ሰው እንደየሃይማኖቱ አስትምህሮ የጽድቅ አክሊልን ለመቀዳጀት ሲል የፈጣሪን ትዕዛዝ ወይም ሕግ የሚያከብር መሆኑን የሚገልጽ ነው። ለምሳሌ፡- አትግደል፣ አትስረቅ አታመንዝር የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ፈጣሪን በሚያመልክ ሰው ዘንድ ክቡር ነው።

ሕገ-መንግሥት የምንለው ደግሞ ሰዎች ማህበራዊ ሕይወትን ከመሰረቱ በኋላ አኗኗራቸውን ሥርዓት ለማስያዝ በስምምነት የሚጸድቁት የጋራ መተዳዳሪያ ደንብ ነው። በዚሁ መሰረት በህግ አርቃቂ፣ በሕግ ተርጓሚና በሕግ አስፈጻሚዎች ቅንጅታዊ አሠራር ተግባራዊ ይሆናል። ሕገ-መንግሥት በሕገ-ልቦና እና በሕገ-እግዚአብሔር መመለስ ያልቻሉ ሰዎችን ከሕገ-ወጥ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ያደርጋል፤ አደብ ያስገዛል።

አሁን በመዲናችን እየታየ ያለው ሕገ-ወጥነት ሶስቱንም የህግ እርከኖች ያለፉ ይመስላል። ሰዎች ሞራል አጥተዋል፤ ፈሪሃ እግዚብሔርም፣ ፈሪሃ መንግስትም አይታይባቸውም። በዛሬው ቅኝታችን ለመመልከት የምንሞክረው በጫኝና አውራጅ ስም እየተደራጁ ህገ-ወጥ ተግባራትን የሚፈጽሙ ሰዎችን ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ ትኩረትን የሚስቡ ሕገ-ወጥ ተግባራት እያሉ እንዴት ጫኝና አውራጆች ላይ ይተኮራል እንዳትሉኝ። እርግጥ ነው ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ፣ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ የሚያደርጉ ሕገ-ወጥ ነጋዴዎች፣ መኪና ከነነፍሱ ሠርቀው የሚሰወሩ ሌቦች፣ በሙስናና በብልሹ አሠራር የተዘፈቁ የመንግሥት ባለስልጣናት እና ሌሎችም እንዳሉ ይታወቃል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችና እግር ጥሏቸው ወደ ከተማዋ የሚመጡ እንግዶችን ካማረራቸው ጉዳይ አንዱ በየጎዳናውና በየመንደሩ እቃ ማውረድና መጫን የምንችለው እኛ ብቻ ነን በሚል በግለሰብ ንብረትና በግል ኪስ የሚያዙ ሕጋዊነትን ሽፋን አድርገው ሕዝብን ስለሚያሰቃዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ስለመኖራቸው ለማንሳት ነው።

እቃ ማውረድና መጫን እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ መታየቱ ባልከፋ። ድንገት መኪና ቆም ብሎ ተሳፋሪን ለማውረድ ሲሞክር ከእረዳቱ ቀድመው መኪና ላይ የሚንጠለጠሉ በየአካባቢው እየተበራከቱ መጥተዋል። ያለባለቤቱ ፈቃድ አስር ኪሎ ግራም የማትሞላ ቋጠሮ ወይም ሻንጣ ብጤ ሁለትና ሶስት ሰው ሆነው ተቀባብለው ካወረዱ በኋላ የሚጠይቁት ገንዘብ እቃው ቢሸጥ እንኳ የማያውጣው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚህ ላይ እራሴ አወርደዋለሁ ወይም እጭነዋለሁ ለሚል ሰው እድል አይሰጡም።

ቀደም ሲል መናኸሪያዎች አካባቢ የሚታየው እንዲህ አይነቱ ድርጊት አሁን በየጎዳናውና በየመንደሩ የሚታይና ሰዎችን ያማረረ ጉዳይ ሆኗል። በሕጋዊነት ስም ከለላ የተሰጣቸው እነዚህ ጫኝና አውራጆች የሚፈጽሙት ዘረፋ በራሱ ላይ ደርሶ ወይም በሌሎች ላይ ሲፈጸም አይቶ ከተማችን ወዴት እየሄደች ነው? ለምን ሕግ የሚያስከብር አካል ጠፋ? የማይል የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ይኖራል ተብሎ አይገመትም።

አንድ መንገደኛ እቃ ይዞ ሲጓዝ ለማስጫኛና ለማውረጃ የሚበቃውን ገንዘብ ተምኖ መያዙ አይቀርም። ድንገት እቃውን ወርረው የያዙ ጫኝና አውራጅ ነን ባዩች ያልጠበቀውን ገንዘብ ሲጠይቁት ዝም ብሎ ሊሰጣቸው አይችልም። በዚህ የተነሳ አላስፈላጊ አምባ ጓሮ ይፈጠርና በገዛ ንብረቱ ስድብና መንጓጠጥ፤ እልፍ ሲልም ቡጢ ሊቀምስ ይችላል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ ደንብ አስከባሪዎችና ፖሊሶች በቅርብ ርቀት ላይ እያሉ ነው። አንዳንዶች አይተው እንዳላየ ሲሆኑ አንዳንዶቹም ሕገ-ወጥ ተግባር የፈጸመውን አካል ሥርዓት ማስያዝ ሲገባቸው ተስማሙ ብለው ሊያደራድሩ ይሞክራሉ። ይህ ሲታይ ሥርዓት አስከባሪዎቹ ከሕገ-ወጡ ቡድን ጋር የጥቅም ትስስር አላቸው እንዴ? ብለን እንድንጠራጠር ያደርገናል።

የቤት ኪራይ ዋጋ 500 ብር ሲጨምርባቸው በቅናሽ ዋጋ ቤት አግኝተው እቃ ጭነው የሚሄዱ ሰዎች የሚደርስባቸው ወከባና እንግልት ደግሞ ከዚህም የከፋ ነው። በማያውቁት መንደር በጎረምሶች ተከበው እስከ አምስት ሺህ ብር እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ምነው ጭማሪውን ከፍዬ እዚያው በተቀመጥኩ የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

ይህ ችግር እዚህ ድረስ የደረሰው በተቆጣጣሪ አካላት ድክመት፣ ወይስ ህዝብና መንግሥትን ለማገልገል ቃል የገቡት የጸጥታ ሃይሎች ለዘብተኝነት? ወይስ እነዚህና ሌሎችም ጉዳዩ ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ነው? ምንም ይሁን ምን ግን እንደዋዛ የሚታዩትና ትኩረት የሚነፈጋቸው ሕገ-ወጥ ድርጊቶች እያደጉ ሄደው የከተሞችን ብሎም የአገርን ገጽታ እንዳያበላሹ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ሰዎች ወጥቶ መግባት ወይም ንብረትን ይዞ መንቀሳቀስ ሥጋት ሆኖባቸዋል። ኢትዮጵያ በተለይም አዲስ አበባ እንደ ደቡብ አፍሪካ ሕገ-ወጦች የሚነግሱባት አገር ከሆነች የዲፕሎማት ከተማ ሆና የመቀጠሏ ነገር አጠያያቂ እንዳይሆን ከወዲሁ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

አንዳንድ ጊዜ ፖሊሶች፣ ደንብ አስከባሪዎችና የጸጥታ ኃይሎች ሕግ ለማስከበር እላፊ ሲሄዱ ይታያል። ለምሳሌ፣ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ የሚካሄድ ከሆነ ስብሰባው ከማደረጉ በፊት ጎዳናዎች ሥነ ሥርዓት እንዲይዙ ይደረጋል። ሕገ-ወጥ የጎዳና ላይ ቤት፣ ሕገ-ወጥ ባለታክሲ፣ ሕገ-ወጥ ነጋዴ፣ የመኪና ሌባ፣ ሞባይል መንታፊ እንዲኖሩ አይፈለግም። ሌላው ቀርቶ ሊስትሮዎች፣ ቆሎ ነጋዴዎች፣ ሶፍትና ማስቲካ ሻጮች አስፋልት ዳር ዝር አይሏትም።

ከዚህ ውጭ ግን ጫኝና አውራጅን፣ የታክሲ ወረፋ አስያዥ ነን እያሉ ህብረተሰቡን የሚያሰቃዩ አደብ እንዲገዙ ሲደረጉ አይታይም። በተለይ በትራንስፖርቱ ዘርፍ የሚታየው ሕገ-ወጥነት ዓይን ያፈጠጠ ነው። የታክሲ ተራ አስከባሪዎች ጉዳይም ከዚህ ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

የአምስት ብር ታሪፍ የሚከፈልበትን መንገድ አስር እና አስራ አምስት ብር እያስከፈሉ ጥቅም የሚጋሩ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። በዚህም ላይ ሁለት ሰው የሚቀመጥበት ወንበር ሶስት ሰው እንዲይዝ ይደረጋል። ትንሽ መሸት ሲል ደግሞ ሁኔታዎቹ ከሚባለውም በላይ የከፉ ይሆናሉ። ታዲያ ሕግ የሚከበረው መች ነው? ታላላቅ እንግዶች ወደ አገራችን ሲመጡ ብቻ ነው? የፖለቲካ ጉዳዮች እየገነገኑ መጥተው ለአገር ስጋት እስከመሆን የሚደርሱት እንዲህ አይነት ማህበራዊ ችግሮች አስቀድመው ባለመፈታታቸው ነውና የሚመለከተው አካል የሕግ የበላይነት እንዲከበር በናፍቆት እየጠበቀ ላለው ህዝብ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ ማሳሰብ እንፈልጋለን።

# ነፃ ሃሳብ

# ተነጋግሮ በመግባባት ለአገራችን ውለታ እንዋል

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ውለታ በብዙ መንገድ ይገለጻል። በተለይ ለአገርና ወገን ሲሆን ደግሞ ትርጉሙ ለየት ይላል። ሁሉም አገር የራሱ ጀግና አለው። እኛም ለአገራችን ውለታ የዋሉ በርካታ የቁርጥ ቀን ልጆች አሉን። ኢትዮጵያ ማንን ትመስላለች ቢባል ህዝቦቿን ከህዝቦቿም ባለውለታዎቿን እላለሁ። አገር የትውልድ ቅብብሎሽ ናት። በዚህ የትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ሁልጊዜም አንድ በላጭ እውነት አለ እርሱም አገርና ህዝብ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከአገርና ህዝብ ከሉዓላዊነትም የበለጠ አንድም ግለሰባዊ ጉዳይ አልነበረም። ዛሬም በዚህ የአገርና ህዝብ እውነት ውስጥ መጓዝ ይኖርብናል። አላማችን አንድ አገር፣ አንድ ህዝብ መፍጠር ከሆነ ከግለሰብና ከቡድን እሳቤ የጸዳች ኢትዮጵያ ታስፈልገናለች።

አሁን ላይ እንወያይ፣ እንመካከር ስንል በአገር አቀፍ ደረጃ እንቅስቃሴ የተጀመረው እኮ ይሄን በብሔርና፣ በሃይማኖት፣ በጎሳና በፖለቲካ ልዩነት የተፈጠሩ ችግሮቻችንን ለማጥበብ ነው። ከእኔነት ስሜት ወጥተን የጋራ አገር ለመገንባት ነው። እኛ አልገባንም እንጂ ተነጋግሮ መግባባት የሰው ልጅ በስልጣኔው የደረሰበት የመጨረሻው የዘመናዊነት ጥግ ነው። ሀያላን አገራት እንዴት ሀያል ሆኑ፣ እንዴት ከኋላ ተነስተው ከፊት ቀደሙ ለሚል ጥያቄ አንድ መልስ ነው ያለው፤ እርሱም በልዩነታቸው ላይ ተነጋግረው ስምምነት ላይ በመድረሳቸው ነው። እኔና እናንተም ስለአገራችን ስንል በችግሮቻችን ላይ ተነጋግረን የጋራ መስማማት ላይ ካልደረስን ከዚህም በላይ ዋጋ መክፈላችን አይቀርም። እኛ ያልገባን ሀያላኖቹ የገባቸው አንድ ነገር ቢኖር የውይይት ጥበብ ነው።

የውይይት ጥበብ ከስልጣኔ ባለፈ ለአንድ አገርና ህዝብ የሰላም ዋስትና ነው። ህልማችን ሰላም ከሆነ፣ ሀሳባችን ስልጡን አገር መፍጠር ከሆነ የውይይትን ጥበብ ወደ ልባችን ማስገባት ይኖርብናል። ተነጋግሮ መግባባትን ባህል እስካላደረግን ድረስ ህልሞቻችንን ሁሉ ውሃ ነው የሚበላቸው። ከችግር ፈጣሪነት ወጥተን ወደ መፍትሄ አመንጪነት መሸጋገር አለብን። የትላንት አዳፋ ታሪኮቻችንን ዘግተን በእርቅና በመተቃቀፍ ኢትዮጵያን ለማሻገር መትጋት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። እኛ ከትላንት እስከዛሬ ችግሮቻችን ላይ እንጂ መፍትሄ ላይ በርትተን አናውቅም። ሀሳቦቻችን ሁሉ ችግር ፈጣሪዎች ሆነው ሲጎዱን ከርመዋል። እንደ ብሔረሰብ ምድር፣ እንደ ብዙሀነታችን የተለያየ ሀሳብ ሊኖረን ይችላል። ልዩነት ለመፍጠር የምንበረታውን ያክል በውይይት አንድነት ለማምጣት ብንበረታ ኖሮ ዛሬ ላይ በዚህ ልክ በሀሳቦቻችን መከራ አናይም ነበር።

ለምሳሌ፣ ቻይናውያን ያስደንቁኛል፤ ቻይና በህዝብ ቁጥር ከዓለም አንደኛ ናት። የዓለምን አንድ ሶስተኛ የህዝብ ቁጥርም የያዘች አገር ናት። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንድ የማይናወጥ አቋም አላቸው፤ ቅድሚያ ለቻይና የሚል። ቻይናውያን እንደ ብዛታቸው ብዙ አይነት ሀሳብ ያላቸው ናቸው፤ በጣም የሚገርመው ደግሞ ያን ሁሉ ሀሳብ ለነውጥ ሳይሆን ለለውጥ፣ ለሽብር ሳይሆን ለብልጽግና ተጠቅመው አገራቸውን በኢኮኖሚ ከዓለም ቀዳሚ አድርገዋል። እኛም ለአንድነታችን ዋጋ ከሰጠን የህዝብ ቁጥራችንን፣ የወጣት ቁጥራችንን ለነውጥ ሳይሆን ለለውጥ መጠቀም እንችላለን።

ወደ ህንድና ወደ አሜሪካ ብትሄዱም ተመሳሳይ ነገር ነው የምታገኙት። ሁሉም ስልጡን አገራት በየትኛውም ጉዳይ ላይ አገራቸውን ያስቀደሙ ሆነው ነው የምናገኛቸው። እኛ አገር ሲሆን ግን ሌላ ነው፤ አንድነታችን የሚታየው ጦርነት ላይና የውጭ አገራት ጣልቃ ገብነት ላይ ነው። በእርግጥ ይህ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን በውስጥ ጉዳዮቻችን አንድነት ይጎለናል። አገር ለመገንባት በምንሮጠው ሩጫ ላይ እኔ ልቅደም እኔ የምንባባል ነን። ሀሳቦቻችን እኔነትን ያረገዙ ናቸው። አምናን እያስታወስን፣ ድሮን እየፈተሸን ዛሬን የምንገፋፋ ነን። እውነት እላችኋለሁ ስልጡን ብንሆን ኖሮ ጊዜ ባለፈባቸው የመቶ አመታት ታሪክ ወደኋላ አስታውሰን አንገፋፋም ነበር። ለእኛ ኋላ ቀርነት ከዚህ የተሻለ ጥሩ ማረጋገጫ አይመጣም። በሀሳቦቻችን ኋላ ቀሮች ነን፤ እናም ዘመናዊነትን ሊያላብሰን የሚችል የሀሳብ ሞገስ ያስፈልገናል።

ሀሳብ ሞገስ ነው፤ ሀሳብ ውርደት ነው። አንዳንዶች በሀሳባቸው ሞገስን አግኝተዋል። እንደእኛ አይነቶቹ ደግሞ በሀሳባቸው ውርደትን ተከናንበዋል። ሀሳብ ድርጊት ነው፣ ድርጊት ውጤት ነው። አሁን ላይ ፍሬአቸውን እየበላን ያሉ ነገሮች ሁሉ በሀሳባችን የተጸነሱ ናቸው። በሀሳባችን ውስጥ ከእኔነት የቀደመ፣ ከትላንት የበረቱ አገራዊ ጉዳዮች እስከሌሉን ድረስ በሀሳባችን መከራ ነው የምንፈጥረው። ማረፊያውን አገር ያደረገ ልብ ክፉ ሀሳብ አያስብም። ስፍራውን ትውልድ ያደረገ አእምሮ መጥፎ ነገር አያደርግም። ሀሳቦቻችን እና ድርጊቶቻችን ሰይጣናዊ የሆኑት በልባችን ውስጥ ከእኔነት የገዘፈ ስፍራ ለአገራችን ስለሌለን ነው።

እንደ ብዛታቸው ቢሆን ቻይናውያን ነበሩ ከየትኛውም አገርና ህዝብ ቀድመው እንደ እያሪኮ የሚፈርሱት። ግን በሀሳባቸው ውስጥ አገር የሚል ስዕል ስለሳሉ፣ በልባቸው ላይ ትውልድ የሚል ጽላት ስለቀረጹ አልፈረሱም። መፍረስ በሀሳብ አለመበርታት ነው። መለያየት ምንም ሊሆን አይችልም ተነጋግሮ አለመግባባት ነው። እንደ አገር ማድመጥን መለማመድ አለብን። እስከዛሬ አድማጭ በሌለበት ስናወራ ነበር፤ ለማድመጥ ሳይሆን ለመመለስ ተዘጋጅተን ስናደምጥ ነበር። እስኪ አሁን ደግሞ ታሪኮቻችንን ቀይረን ለመግባባት እናድምጥ፣ ለመስማማት እንናገር። እንልመድ።

ትላልቅ ተአምራቶች የሚፈጠሩት በመደማመጥ ውስጥ እንደሆነ የገባን ጥቂቶች ነን። የተናገርነውን ያክል ብናደምጥ፣ የተሰበሰብነውን ያክል ወደ ተግባር ብንገባ ዛሬ ሌላ ነበርን። እመኑኝ በልባችን ውስጥ አንድነትና ወንድማማችነት ካለ ሀሳቦቻችን ጎጂዎች አይሆኑም። ለማድመጥ እንጂ ለመናገር አንበረታም። እንደ አገር እያጠቃን ያለው ነገር አለመደማመጥ ነው፤ ካለመደማመጥም አለመግባባት ነው። ለመግባባት ማድመጥ ያስፈልጋል። ለመደማመጥ ደግሞ የጋራ ህልምና ራዕይ ግድ ይለናል። ህልምና ራዕዮቻችንን በብሔርና በጎሳ፣ በፖለቲካና በሃይማኖት ከፋፍለን የምናመጣው የጋራ ብልጽግና የለም። ከሁሉ አስቀድመን ለመስማማት መነጋገር፣ ለመነጋገር መደማመጥ ይኖርብናል። አገር ህዝብና ትውልድ ያሉበትን የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ውስጣችን ማስረጽ ይጠበቅብናል።

ለአገር ውለታ መዋል የዜግነት ግዴታ ነው። መንግስት ብቻ አይደለም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ አይደሉም፣ ባለሀብቶችና ባለስልጣናት አይደሉም ሁላችንም ለአገር ውለታ የመዋል ግዴታ አለብን። ውለታዎቻችን ደግሞ ተነጋግሮ በመግባባት የሚጀምሩ ናቸው። ተነጋግረን ሳንግባባ ለራሳችንም ሆነ ለአገራችን ውለታ መዋል አንችልም። ሰላም ያለው ንግግር ውስጥ ነው። እድገት ብልጽግና ያለው ውይይት ውስጥ ነው። አገርና ትውልድ የሚፈጠሩት በጋራ ሀሳብ ውስጥ ነው። እንደ አገር ይሄን ትልቅ ጸጋ ሳንጠቀምበት ከወንድሞቻችን ጋር እየተገፋፋን አይጥና ድመት ሆነን ቆይተናል። እነዚያ ጊዜያቶች ኢትዮጵያን ለመሳል፣ ትውልዱን አርነት ለማውጣት በቂዎች ነበሩ። እነዚያ ጊዜያቶች ለራሳችንም ሆነ ለአገራችን ውለታ የምንውልባቸው ነበሩ ግን ባለማወቅ ሳንጠቀምባቸው ቀርተናል።

ያለፈውን ጊዜ ማስረሻ ይሆኑን ዘንድ ዛሬን በእርቅና በንግግር መጀመር ለህዳሴአችን አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው። እየኖርን ያለነው በአባቶቻችን ውለታ ነው። የአባቶቻችን የአንድነት መንፈስ ዛሬን እንድናይ እድል ሰጥቶናል። መጪው ትውልድ በእኛ የእርቅና የድርድር ፍኖት ነገ ላይ ብርሃን እንዲያይ ለውይይት የበረታ ልብና አእምሮ ያስፈልገናል። አገር የትውልድ ቅብብሎሽ ናት ያልኳችሁ ለዚህ ነው። ከአባቶቻችን የተቀበልናትን የአንድነትና የጽናት ምድር፣ የእውነትና የፍትህ፣ የነጻነትና የእኩልነት አገር ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ የዜግነት ግዴታ አለብን። ይሄ የአባቶቻችን አደራ በእኛ ላይ ይገለጽ ዘንድ በራስ ወዳድነት ያጠፋናቸውን ኢትዮጵያዊ ጸዳሎቻችንን መመለስ አለብን። በማን አለብኝነት ያቆሸሽናቸውን መልኮቻችንን ማደስ አለብን። በጦርና በጠመንጃ፣ በሀይልና በጉልበት የመጣንባቸውን የኋላ ቀርነት ጎዳናዎች መቀየር አለብን። ባለመደማመጥና ባለመግባባት የተጓዝንባቸውን ረጅም የብቻ ጉዞዎች መሻር አለብን። ኢትዮጵያ በነዚህ ውስጥ የለችም። የምንናፍቃትን አገር፣ የምንናፍቀውን ትውልድ ፈልገን ያጣነው በዚህ ውስጥ ስለቆምን ነው። ዛሬ ላይ ብዙ እያለምን፣ ብዙ እየተመኘን ያልተሳካልን በነዚህ አዳፋ እውነቶች ውስጥ ስለጎለመስን ነው። ዛሬ ላይ ለራሳችንም ሆነ በዙሪያችን ላሉት ውለታ መዋል ያቃተን እውቀታችን የክፉት እውቀት ስለሆነ ነው።

ወደፊት ለመራመድ ከማጡ መውጣት አለብን። ብርሃን ለማየት ጨለማዊ አስተሳሰቦቻችንን ማጽዳት ይኖርብናል። ለዘመናት በማይጠቅሙን እኩይ ነገሮች ላይ ነበርን፣ መንገዳችን ላይ እንቅፋት እያስቀመጥን ወደፊት ለመሄድ ስንጥር ነበር። ባለመስማማት ሁሉ ነገራችንን ያጣንበት ጊዜ ነበር። አሁን ግን ይበቃል፤ እነዛ ጊዜዎች ለእያንዳንዳችን የባከኑ የመከሰር ጊዜያቶች ነበሩ። አሁን በመነጋገርና በጋራ ሀሳብ የባከንበትን ጊዜ የምንክስበት የእርቅ ጊዜ ይሁን። የመደማመጥ፣ የምክክር ጊዜ ይሁን። አገራችን ምን እንደምትፈልግ እንጂ እኛ ምን እንደምንፈልግ የምንጠይቅበት ጊዜ የሚያበቃበት ትክክለኛ ጊዜ አሁን ይመስለኛል። ለአገራችን ውለታ ለመዋል ዛሬ ከየትኛውም ጊዜ በላይ ተመራጭ ነው። እንደ አገር መንግስት ለዘላቂ ሰላም ሲል ችግሮቻችንን በውይይት የምንፈታበትን አገራዊ ምክክር ይፋ አድርጓል። በዚህ እድል በመጠቀም የማያግባቡንን ነገሮች በመለየትና መፍትሄ በመስጠት ወዳላደረስንበት የከፍታ ጉዞ መሄድ ቀጣይ አላማችን መሆን አለበት። ካለንበት ሳንቀሳቀስ እዛው እየረገጥን የምናመጣው አገራዊ በረከት የለም። ከአምና ዘንድሮ መማር አለብን፣ ጥፋቶቻችን አስተማሪዎቻችን ሆነው ለተሻለ ድል ሊያበቁን ይገባል።

እኛ የቆምንው ሳይነጋገሩ በተግባቡ አባቶቻችን ሀቅ ላይ ነው። እኛ የቆምንው ኢትዮጵያን ብለው ስለ ስሟ በተንገላቱ ባለውለታዎቻችን ላይ ነው። ታዲያ እንዴት እኛ ተነጋግሮ መግባባት አቃተን? እንዴት ስለአገራችን አንድ አይነት ሀሳብ፣ አንድ አይነት ምኞት አጣን? ለአገራችን የእኛ ውለታ ምንድነው? እንደ ዜጋ፣ እንደ መንግስት፣ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ምን እያደረግን ነው ያለነው? እኚህ ጥያቄዎች መልስ ያሻቸዋል። ለአገራችን ውለታ የምንውለው የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ስናውቅ ብቻ ነው። የዛሬዋን ኢትዮጵያ በክብርና በነጻነት ያቆሙ አባቶቻችን በኢትዮጵያዊነት ብቻ የተግባቡ ነበሩ። በሰውነት ዋጋ ያወጡ ነበሩ። ወደእኛ ሲመጣ ይሄ እውነት የከሰረ ሆኖ እናገኘዋለን። ኢትዮጵያዊነት እያግባባን አይደለም። ሰውነት ዋጋ አጥቶ ብዙ ቦታ ላይ አይተናል። የአባቶቻችን አይነት ኢትዮጵያዊ እውነት፤ የአባቶቻችንን አይነት የሰውነት መንፈስ ያስፈልገናል።

የአገር ክብር በብሔርና በፖለቲካ አይመዘንም። የአገር ክብር በግለሰብና በቡድን እኔነት አይለካም። የአገር ክብር መመዘኛው ህዝብ ነው፤ ትውልድ ነው። የአገር ክብር መለኪያው የአንድነትና የጋራ መንፈስ ነው። የራቁ ታሪኮቻችንን እያስታወስን በትውልዱ ላይ እሳት ማንደድ ተገቢ አይደሉም። ዳግም ወደማንመለስበት ተነጋግሮ የመግባባት፣ ተግባብቶ የመስማማት ከፍታ ላይ መውጣት አለብን። ዳግም ወደማንመለስበት የአንድነት ስልጣኔ መሸጋገር አለብን። ያለ ምንም ቅደመ ሁኔታ ሰላም ያስፈልገናል፣ እርቅ ግድ ይለናል። አገራችን ከሰላም ሌላ ሁሉንም አይታለች፤ የሰላም ርሀብ ለትውልዱ የህልውና ድርቀት ነው። የሰላም እጦት ለህዝቦች የስጋት ምንጭ ነው። እንደ አገር ደግሞ ሁሉንም አይነት ዋጋ የሚያስከፍል ሁሉንም አይነት ክስረት ነው። ይሄን ድርቀት፣ ይሄን ስጋት፣ ይሄን ክስረት በንግግር መመለስ አለብን። ያኔ ለውዷ አገራችን ውለታ እንውላለን። ለዛሬው አበቃሁ፤ ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ታዳጊ የፈጠራ ባለሙያዎች እና ዲጂታል ሽግግር

**ዳግም ከበደ**

ዲጂታል ኢትዮጵያ 225ትን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ስትራቴጂ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ አኳያ በዘርፉ ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ እንደ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ያሉ ተቋማት የዲጂታል ክህሎት ትምህርቶችን በራስ አቅምና ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር እየሰጡ ይገኛሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ዶክተር ዐቢይ አሕመድ “ዓለም ባልተጠበቀ ፍጥነት አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት እያካሄደች ትገኛለች” በማለት ማህበረሰቡ ከዚህ ክስተት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማረጋገጥ እና ወጣቶቻችን በአዲሱ የዓለም ሥርዓት ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ኢትዮጵያ በንቃት መሥራት እንደሚጠበቅባት ያሳስባሉ። በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት እንደ የሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence)፣ የበይነ መረብ ቁሶች (Internet of things)፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ እና ትልቅ ውሒብ (Big Data) ባሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የሚደገፉ የማምረት፣ የመገናኛ እና የአኗኗር ዘዬ ሽግግርን ለማካሄድ የኢትዮጵያ መንግስት ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ መሆኑን “በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025” ስትራቴጂ ላይ ይፋ አድርገዋል። “ታዳጊዎች አዳዲስ ክሂሎት እና ዕውቀቶችን ይፈልጋሉ፤ የወደፊቱን ጊዜ በተሻለ ለመጠቀም እንዲችሉ የማድረግ ደግሞ የእኛ ኃላፊነት ነው” የሚሉት ወጣቶች የፈጠራና የቴክኖሎጂ ክህሎታቸውን የዳበር እቅድን ነድፎ እየተገበረ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል።

የትምህርት ተቋማት የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀታቸው የላቀ ወጣቶችን በፈጠራ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ ከሚሰሩት ተግባር ባሻገር አዲሱ ትውልድ በግል በሚያደርገው ጥረት በርካታ ችግር ፈቺ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ክህሎቶችን እያወጡ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ የፈጠራ ስራዎች በባለሃብቶችና በሚመለከተው የመንግስት አካል ድጋፍ አግኝተውና ወደ ማህበረሰቡ ደርሰው ሲያገለግሉ አይታዩም። ይሄ በሚመለከታቸው አካላት ትኩረት አግኝቶ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ቀደም ካሉት ግዜያት በተሻለ ወጣት የፈጠራ ባለሙያዎች ተነቃቅተው ክህሎታቸውን በመጠቀም የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎችን በየጊዜው ሲያስተዋውቁ ይስተዋላል።

በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከሰማናቸው ስኬታማ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶች ውስጥ ለምሳሌ ያክል ለማንሳት ስንሞክር፤

በደብረ ብርሃን ከተማ በኤሌክትሪክ ኃይል የምትሰራ እና አራት ሰዎችን የመጫን አቅም ያላት ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ (ባጃጅ) በአንድ ስራ ፈጣሪ መሰራቷ መግለፅ ይቻላል። የተሽከርካሪዋ አምራች አቶ መቅድም ኃይሉ ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪዋ በአብዛኛው አገር ውስጥ የሚገኙ ግብዓቶችን በመገጣጠም ነው የተሰራችው። በወርክ ሾፓቸው የተሰራችው ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዋ በማንኛውም የኤሌክትሪክ ቻርጀር ለ3 ሰዓታት ቻርጅ ተደርጋ በሰዓት 40 ኪሎ ሜትር መጓዝ የምትችል እንደሆነች ማወቅ ይቻላል። በኤሌክትሪክ ሃይል የምትሰራው ይህች ባለሦስት እግር ተሽከርካሪ ሾፌሩን ጨምሮ አራት ሰዎችን የመጫን አቅም ያላትና ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያውያን የፈጠራ ባለሙያ የተሰራች ስኬታማ የቴክኖሎጂ ውጤት እንደሆነች መረዳት ይቻላል።

በተለያየ ጊዜም በወጣት የፈጠራ ባለሙያዎች የሰው አልባ ድሮን፣ አውሮፕላኖችና መሰል የዲጂታል ቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች መሰራታቸውንም መረጃዎች ያመላክታሉ። እነዚህ የፈጠራ ውጤቶች በ2025 ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራተጂ ትግበራን ለማሳካት ከሚያግዙ ክህሎቶች አንዱ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። ለዛሬም የዝግጅት ክፍላችን በዚህ አምድ ላይ መንግስት በልዩ ትኩረት ይዞ ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር እየሰራ የሚገኘውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ክህሎት ባለሙያዎችን የመደገፍ ስራን የሚያመላክት ጉዳይ ለማንሳት ወድደናል። በዋናነትም ሁለት ወጣትና በትምህርት ላይ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ፈጣሪ ወጣቶችን በእንግድነት በማቅረብ ክህሎታቸውን ተጠቅመው



ተማሪ በፀሎት በቀለ



ተማሪ ዘካሪያስ ወንዳፍራሽ

የሰሯቸውን የፈጠራ ውጤቶች እናስተዋውቃችኋለን።

ታዳጊ የፈጠራ ባለሙያ ተማሪ በፀሎት በቀለ በአቤኔዘር ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነች። ታዳጊዋ የኮንስትራክሽን ዘርፉን የሚያግዝ የመገናኛ ዘዴ (ፕላትፎርም) እንደሰራች ትናገራለች። ይህም በቀላሉ ኮንትራክተሮች እንዲሁም ኢንጂነሮች ከደንበኞቻቸው ጋር በቀላሉ መገናኘት የሚችሉበት መንገድ መሆኑን ትገልፃለች።

የቴሌግራም ማህበራዊ መተግበሪያን በመጠቀምና በውስጡ “ቦት” በሚባለው መንገድ የፈጠራ ስራዋን ደግፋ የሰራችው ታዳጊዋ በቀላሉ ግንኙነት የሚፈጠርበትን አማራጭ መስራት ችላለች። “በአገራችን የኮንስትራክሽን ዘርፍ የተማሩ ወጣቶች ተመርቀው ያለስራ ተቀምጠዋል” የምትለው የፈጠራ ባለሙያዋ በፀሎት ባለሙያዎቹ በመንግስት ፍቃድ ያላቸው ቢሆንም ከአሰሪዎች ጋር ለመገናኘት እንደሚቸግራቸው ትገልፃለች። በተጨማሪ አሰሪዎችም ቤት ከማሳደስ አንስቶ ትላልቅ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር ሁነኛ ባለሙያ ማግኘት እንደሚቸግራቸውና የግንኙነት መንገዱ እክል ያለበት መሆኑን ትናገራለች። በዚህ ምክንያት ክፍተቱን ለመሙላት በማሰብ ፕላትፎርሙን ለመፍጠር እንዳነሳሳት ትገልፃለች።

“ይህ ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ ላይ ሆነን በሀዋሳ ከተማ ሳይቶችን ለመገንባት አሊያም ባለሙያዎችን ለማግኘት ብንፈልግ በቀላሉ የስራ ልምድና ሌሎች ዶክመንቶችን ማግኘት እንችላለን” የምትለው ታዳጊዋ የፈጠራ ባለሙያ እርቀት ሳይገድብ የግንኙነት አድማስን ለማስፋት በማሰብ ፕላትፎርሙን መፍጠር እንደቻለች ታስረዳለች። በተለይ ህጋዊ ውል ለመፈራረምና ምቹ የመግባቢያ መንገድ መሆኑንም ታስረዳለች።

“መተግበሪያው በርካታ ፋይዳዎች አሉት” የምትለው በፀሎት በዚህ ቴክኖሎጂ ደንበኞችና ባለሙያዎች ግንኙነት መፍጠር ከቻሉ ለበርካታ ሰዎች የስራ እድል መፍጠር እንደሚያስችል ትናገራለች። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብዙ ሳይቶችን ይዘው ስለሚሰሩ ወደ ክፍለ አገር ወጥተው ከደንበኞች ጋር ውል ለመፈፀም ፍላጎት ላይኖራቸው እንደሚችል በመግለፅ ይህ የግንኙነት መድረክ ግን በዚያው አካባቢ የሚገኙና የተማሩ ኢንጂነሮችን ከደንበኞች ጋር የማገናኘቱን እድል እንደሚፈጥር ትናገራለች።

ታዳጊ በፀሎት ይህን ፕላትፎርም ወደ አፕሊኬሽንና ዌብሳይት ለመቀየርና ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን እየሰራች እንደሆነ ትናገራለች። ይህ የፈጠራ ስራዋ በሁሉም ወገኖች ተደራሽ የሚሆን ከሆነ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ መፍጠር የሚችል መሆኑን ትገልፃለች። በቀጣይ የሶፍትዌር ኢንጂነር በመሆን መሰል የፈጠራ ስራዎችን ማበርከት እንደምትፈልግ ተናግራም ለዚህ ውጤታማ ስራዋ የራይድ የትራንስፖርት አገልግሎት የፈጠረችው የቴክኖሎጂ ግንኙነት ትልቅ መነቃቃት እንደፈጠረላት ገልፃለች።

“ታዳጊዎች በተለይ ሴቶች መበረታታት አለባቸው” የምትለው ተማሪና የፈጠራ ባለሙያ የሆነችው በፀሎት ማህበረሰቡ ይህን መሰል ክህሎት ያላቸውን ልጆች የሚደገፉበትን ምቹ አጋጣሚዎች ሊፈጥር እንደሚገባ ትናገራለች። በተለይ መንግስትም ሆነ የትምህርት ተቋማት የቴክኖሎጂ ምቹ መሳሪያዎችን እንዲሁም ሌሎች መሰል ድጋፎችን እንዲያደርግ ትጠይቃለች።

ሌላኛው የፈጠራ ባለሙያ ተማሪ ዘካሪያስ ወንዳፍራሽ ይባላል። የህክምና ዘርፍ ላይ በተለይ ደግሞ ለአይን ህክምና ሙያ የሚያግዝ ዲጂታል የፈጠራ ውጤትን አስተዋውቋል። በተለይ በኢትዮጵያ የህክምና ዘርፍ ላይ በአገር በቀለ የፈጠራ ውጤቶች የህክምና መሳሪያዎችን የመፍጠር ልምድ ባለመኖሩ የእርሱ የፈጠራ ውጤት በርካታ ነገሮችን እንደሚያቀል ይጠበቃል። በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገቡ መሳሪያዎችን ለማስቀረት እርሱን መሰል ባለሙያዎችን ከማበረታታት ባለፈ በባህላዊ መንገድ የሚተገበሩ ዘዴዎችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለመቀየር የሚደረገውን ጥረት እንደሚያግዝ ጥርጥር አይኖረውም።

ታዳጊ የፈጠራ ባለሙያው ዘካሪያስ በዓይን ህክምና ውስጥ “አክታምቦሎጂ” በመባል የሚታወቀውን የዓይን እይታ መፈተሻ መንገድ ዲጂታላይዝ በማድረግና ቀደም ሲል የነበረውን ክፍተት በመሙላት፣ የስሌት ጊዜው የሚወስደውን ጊዜ እንዲቆጥብ በማድረግ በአዲስ መልክ ማስተዋወቅ ችሏል። በተለይ የዓይን እይታቸው የቀነሱ ሰዎች የሚገኙበትን ደረጃ ከማሳየቱም ባለፈ የመንጃ ፍቃድ ለማውጣት በርካታ ሰዎች የሚወስድባቸውን ጊዜ እንደሚቆጥብ ነው የሚናገረው።

“የእይታ መለኪያ ማሽኑ በቀላል ወጪ የተሰራና ከውጭ የሚመጡ ማሽኖችን የሚያስቀር ነው” የሚለው ታዳጊው የፈጠራ ባለሙያ፤ አጠቃላይ ወጪው 2ሺ800 ብር እንደሆነ ገልጾ ከውጭ የሚገባው ግን እስከ 14ሺ ብር እንደሚፈጅ ነው የሚናገረው። ከዚህ አንፃር ታዳጊው የሰራው ይህ የዓይን እይታን መለኪያ ዲጂታላይዝድ ማሽን ወደ ትግበራ የሚገባ ከሆነ በርካታ ነገሮችን እንደሚያቀል መገንዘብ ይቻላል።

የዲጂታል የዓይን እይታ ደረጃ መለኪያው በቀላሉ በታካሚው በራሱ ቁጥጥር የሚተገበር ሲሆን ውጤቱ ግን ሚስጢራዊ በሆነ መንገድ ወደ አካሚው (ነርስ ወይም ዶክተር) በመግባት ቀልጣፋና ተዓማኒ ውጤትን የሚያስተላልፍ ነው።

የታዳጊ ዘካሪያስ የፈጠራ ስራ የሆነው የአይን ህክምና መሳሪያ ለማምረትና በሁሉም የህክምና ጣቢያዎች ለማደረስ ቀላል እንደሆነ ይናገራል። በተለይ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙ ጤና ጣቢያዎች፣ ጤና ኬላዎች እንዲሁም የመንግስትም ሆነ የግል የጤና ተቋማት ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ወጥቶበት ከሚመጣው መሳሪያ ይልቅ የእርሱን የፈጠራ ውጤት በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንደሚችሉ ያስረዳል።

“ወደፊት በህክምና ዙሪያ ላይ ያሉ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎችን መስራት እፈልጋለሁ” የሚለው ታዳጊው የፈጠራ ባለሙያ ዘካሪያስ በተለይ በህክምና የክፍያ ስርዓትና አላስፈላጊ ብክነት ላይ አንድ የፈጠራ ውጤት ለማበርከት ፍላጎት እንዳለው ይናገራል። ይህ ብቻ ሳይሆን በህክምና ሂደት ላይ ያሉ ማንኛውንም አሰራሮች ዲጂታላይዝድ ለማድረግና የአሰራር ስርዓቶቹን ለማዘመን እንደሚተጋ ይናገራል። ይህን መሰል ህልም ያላቸው ታዳጊዎች ስኬታማ እንዲሆኑ መንግስትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻል። አሁን ላይ ግን ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ የፈጠራ ባለሙያዎችን የሚያበረታቱ ጅምር ሙከራዎችን እንዳሉም ተናግሯል።

### እንደ መውጫ

የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 የትግበራ ሂደት የሚሳካው መሰል ታዳጊ ፈጣሪ ባለሙያዎችን ማበረታታት ሲቻል እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን ያምናል። በአገሪቱ ባሉ በሁሉም የትምህርት ተቋማት ውስጥ ብሩህ አእምሮ ያላቸው ታዳጊ ተማሪዎች እንዳሉም እንዲሁ። ለእነዚህ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠር ለተያዘው የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሽግግር መሳካት የራሱን ድርሻ እንደሚጫወት መገመትም የሚከብድ አይደለም።

በተጨማሪ በዲጂታል ስትራቴጂው የአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳው ግብርናን፣ ማኑፋክቸሪንግን፣ ማዕድንን፣ ቱሪዝም ፣ አይሲቲ እና የፈጠራ ኢንዱስትሪው የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ የመረጣቸው ዘርፎች ሲሆኑ፤ እነዚህ ዘርፎች የስራ እድል እንዲፈጥሩ፣ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኙ እና አካታች እድገትን ዕውን እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ መሰል የፈጠራ ውጤቶችን ማበረታታት እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ በርካታ ወጣቶችና ታዳጊዎች ብቁ ክህሎት እንዲኖራቸው ለማስቻል መስራት አስፈላጊ ነው እንላለን።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ሕጎቹ እንዲዘገዩ ወይስ እንዲቀሩ?

**ታምራት ተስፋዬ**

ለአሜሪካ ሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት የቀረበው ኤች አር 6600 የተሰኘ ረቂቅ «የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት ለማረጋገጥ እንዲሁም ዲሞክራሲዋን ለማፅናት የወጣ ሕግ» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። በቅርቡ ከመፅደቅ እንዲዘገይ ሆኗል የተባለው ይሕ ረቂቅ ሕግ በኢትዮጵያ ግጭቶች እንዲቆሙ ይጠይቃል።

በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸውና በኢትዮጵያ ላይ እየደረሱ ናቸው የተባሉት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዲያበቁ ብሎም ጥሰቶች የፈፀሙ ሁሉ ተጠያቂ እንዲደረጉም ይጠይቃል። ሰላማዊት ዲሞክራሲም የሰፈነባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ሁሉን አካታች ውይይት እንዲደረግ ረቂቅ ሕጉ ይጠይቃል። ይሕ ካልሆነ በአንፃሩ የአሜሪካ መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን እንደሚወስድ በሕጉ በዝርዝር ተጠቅሷል።

የኤች አር 6600 እና የኤስ 3199 ረቂቅ ሕጎችን በሚመለከት ሃሳባቸውን የሚያጋሩ ምሁርንም በአንጻሩ፤ «ረቂቅ ሕጉ የኢትዮጵያን ህልውናና ነጻነት የሚዳፈር ብቻ ሳይሆን ማዕከላዊው መንግስት እንዲዳከምና ኢትዮጵያ የሊቢያን መንገድ እንድትከተል ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ አደገኛ ነው» ይሉታል። ረቂቅ ሕጎቹ ተቀባይነት አግኝተው ተፈጻሚ የሚሆኑ ከሆነም ኢትዮጵያ ላይ በተለያዩ መስኮች ከፍተኛ ተጽዕኖን ሊያስከትሉ እንደሚችል እየገለፁ ናቸው።

የኤች አር 6600 ሕግ በረቂቁ ኢትዮጵያን የሚያዳክምና በአፍሪካ ቀንድ አለመረጋጋትና ቀውስ እንዲፈጠር የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር በፋይናንሱ ዘርፍ ኢትዮጵያ የምታገኘውን የብድር፣ ዕርዳታና መሰል ጥቅማ ጥቅሞች ማስቀረትን ያለመ መሆኑ ያመላክታሉ።

አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምታደርገውን የደኅንነትና የንግድ ድጋፍ እንድታቆም እንዲሁም ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ አበዳሪዎችና የገንዘብ ምንጮች (አይ ኤም ኤፍና የዓለም ባንክን ጨምሮ) ገንዘብ እንዳታገኝ እስከ ማድረግ የሚደርስ ዕርምጃም ተካቶበታል።

በኢንቨስትመንት ዘርፍ ደግሞ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ፋይናንስ ኮርፖሬሽኖች ጋር ያላትን ግንኙነት በማገድ ኢንቨስትመንቶችንና የገንዘብ ልውውጦችን የማስቆም አቅም አለው። ረቂቅ ሕጉ መሰረታዊ መብቶችንም ያግዳል።

«ይህ ሕግ ከጸደቀ የአገሪቱ ኢኮኖሚን በከፍተኛ መልኩ በማድቀቅ በእያንዳንዱ ዜጋ ኑሮ ላይ ከባድ ጫና በማድረስ እጅግ አደገኛ ሁኔታን የሚፈጥር ነው» ይላሉ። ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ለማከናወን የውጪ የፋይናንስ ድጋፎችን እንደምትቀበል የሚገልጹት የምጣኔ ሃብት ምሁራንም፤ በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድ ግንባታ ዙሪያ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ለማስቀጠል ብድር ያስፈልጋል። ይህ ረቂቅ አዋጅ ኢትዮጵያ መሠረተ ልማት ግንባታዋን እንዳታስቀጥል እክል የሚፈጥር ከሆነ ተጎጂው መንግሥት ሳይሆን ተራው ዜጋ ነው» ይላሉ።

በአሁን ወቅትም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚገኙ የአሸባሪው ቡድን ትሕነግ ደጋፊዎች ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተቀመሩት ኤች አር 6600 እንዲሁም ኤስ 3199 የተሰኙ ረቂቅ ሕጎች እንዲጸድቁና የሚፈልጉት እንዲሆን ተግተው እየሰሩ ናቸው።

በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንም የኢትዮጵያ ወዳጆችም በሌላ በኩል ፊርማዎችን በማሰባሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፣ ሕጉን የሚደግፉ የኮንግረሱን አባላት በማነጋገርና ተቃውሞዎችን በማሰማት ረቂቅ ሕጉ እንዳይጸድቅ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ላይ ተጠምደዋል። በተለያዩ ከተሞች ታላላቅ የተቃውሞ ሰልፎችን በማካሄድ ረቂቅ ሕጉ ለአሜሪካም ሆነ ለኢትዮጵያ የማይጠቅም መሆኑንም በህብረት አስተጋብተዋል።

በአሁን ወቅት ረቂቅ ሕጎቹ ከነበሩበት የ8ተኛ ደረጃ አጀንዳነት ወደ 335ተኛ ወርደዋል። እንዲዘገዩ መደረጉም በኢትዮጵያ በኩል ደስታን ፈጥሯል። በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አቶ እንዳለ ንጉሴ፣ ረቂቅ ሕጎቹ ለጊዜው ባሉበት እንዲቆዩ የሚል ሃሳብ መንፀባረቁ የኢትዮጵያውያን ብርቱ ርብርብ ውጤት ስለመሆኑ ይመሰክራሉ። ይሑንና ባሉበት እንዲቆዩ ተደርገዋል ማለት ፋይላቸው ተዘግቷል ማለት እንዳልሆነ ያስገነዝባሉ።

> “
>
> **እነዚህ ረቂቅ ሕጎች በውጭ ሽፋናቸው ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ልማትና መረጋጋት የሚያስቡ ይምሰሉ እንጂ ውስጣቸው ሲገለጥና ይዘታቸው ሲፈተሽ በጣም አደገኛ፣ የኢትዮጵያን ህልውና የሚፈታተኑና አገሪቱን በእጅጉ የሚያዳክሙ ብሎም የሚጎዱ ናቸው**
>
> ”

እንደ አቶ እንዳለ ሁሉ በጉዳዩ ላይ ሃሳባቸውን የሚያጋሩ ምሁራንም «ረቂቅ ሕጎቹ ባሉበት እንዲቆዩ መደረጉ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ትልቅ ስኬት ነው። ይሑንና ረቂቅ ሕጉ እንዲቆይ መደረጉ በራሱ ሙሉ ድል አይደለም። እንዲቆይ መደረጉም ብቻውን ጥቅም የለውም።» ይላሉ።

«አንድ መታወቅ ያለበት አብይ ጉዳይ ቢኖርም ረቂቅ ሕጎቹ ተራዘሙ ማለት ተሰረዙ ማለት አይደለም፤ ረቂቅ ሕጎቹ የተጠመዱና ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲፈነዱ የተደረጉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል፣ ደጋግሞ መቃወም የግድ ነው። መዘናጋት ፈፅሞ ሊታሰብ አይገባም» ሲሉ ያስጠነቅቃሉ። አንዳንዶች በአንፃሩ ረቂቅ ሕጎቹ እስካልተሰረዙ ድረስ ጠረጴዛችን ስር ናቸው እንዲህ ካላደረጋችሁ እንዲህ እናደርጋለን በሚል ማስፈራሪያ እጅ ለመጠምዘዝ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ እንደሆኑም ያስገነዝባሉ።

ሕጎቹን በሚመለከት አንዳንዶች፣ ሕጎቹ ኢትዮጵያ ላይ ሳይሆን የጊዜው መንግሥት ላይ ጫና ማሳደርን አላማ ያደረጉ ናቸው በሚል ሙጉት ሲገጥሙ ይስተዋላል። ይሕን እሳቤ የሚደግፉት እንዳሉ ሁሉ በርካቶች ይቃወሙታል። አንዳንዶች በአንፃሩ እሳቤው ፍፁም ስህተት መሆኑን በማስረገጥ አምርረው ይቃወሙታል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን ግርማ፣ አንድ መጽሐፍ በሽፋኑ ወይንም በርእሱ ሳይሆን በይዘቱና ውስጡ ባለው ትሩፋት እንደሚመዘን ሁሉ፣ ይህን ሕግ ጠንቅቆ ለመረዳት ውጪውን ሳይሆን ውስጡን መፈተሽ የግድ ስለመሆኑ አጽእኖት ይሰጡታል።

«እነዚህ ረቂቅ ሕጎች በውጭ ሽፋናቸው ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ልማትና መረጋጋት የሚያስቡ ይምሰሉ እንጂ ውስጣቸው ሲገለጥና ይዘታቸው ሲፈተሽ በጣም አደገኛ፣ የኢትዮጵያን ህልውና የሚፈታተኑና አገሪቱን በእጅጉ የሚያዳክሙ ብሎም የሚጎዱ ናቸው»ይላል።

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አቶ እንዳለ ንጉሴ፣ ረቂቅ ሕጉ «ኢትዮጵያ ውስጥ መረጋጋት፣ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ» በሚል ሽፋን በዜጎች ብርቱ ትግል የወደቀውን የሽብር ቡድን እንደገና እንዲያንሰራራ በማድረግ አገሪቱን የመከፋፈል አጀንዳ የያዘ ነው» ይላሉ።

የረቂቅ ሕግ መነሻ አይን ያወጣ የቅኝ ልግዛህ ወይንም የኒዎኮሎኒያሊዝም አስተሳሰብ በመሆኑ አዋጁን የሚያዘጋጀው ቡድን በኢትዮጵያውያን ዘንድ አንድነት እንዳይኖርና ሕዝቦቿን የመከፋፈል አጀንዳ የነገበ ስለመሆኑን ይጠቁማሉ።

«እነዚህ ሕጎች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሆን ተብለው የተቀመሩ ሴራዎች መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ ምሁራን፤ ሕጎቹ እንዲፀድቁ እድል መስጠት የሚጎዳው ፖለቲካውን፣ መንግሥትን ወይም ባለስልጣንን ሳይሆን አገርና ሕዝብን ነው»ይላሉ።

መንግሥትና በአመራር ላይ የሚገኝ ግለሰብን አዳክማለሁ በሚል አገርን ለጥፋት የመዳረግ ግዙፍ ስህተት መሆኑን መረዳት እንደሚያስፈልግም አፅእኖት ይሰጡታል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የአሜሪካ ማዕቀብ የሚጎዳው በድህነትና በግጭት የቆየውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ስለመሆኑ ያሰምሩበታል።

መንግሥታት በየጊዜው ቢቀያየሩም አገር ግን እንደማትቀየር እና በውጭ ጣልቃ ገብነትና ሴራ ደካማ መንግሥት ተፈጥሮ ጠንካራ አገር እንደማይኖር ታሳቢ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚያስገነዝቡት ምሁራኑ፤ የሕጎቹ መሰረዝ ሕዝብና አገር ላይ ከሚያስከትለው መጠነ ሰፊ ጉዳት አንፃር የሕጉቹ እንዲዘገዩ መደረግ ሳይሆን መሰረዝ የግድ መሆኑን ያሰምሩበታል።

አንዳንዶች በአንጻሩ ለሕጎቹ መሰረዝ መንግሥትም የራሱን የቤት ሥራ መወጣት እንዳለበት አጽእኖት ይሰጡታል። በተለይ ሰብአዊ መብትን በማክበር እና በማስከበር ረገድ መንግሥት ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንዳለበት ያስገነዝባሉ። የሕግ ባለሙያው አቶ ካሳሁን ሃይሌ ይሕን እሳቤ ከሚጋሩት መካከል አንዱ ናቸው።

ኢትዮጵያ በረቂቅ ሕጉ የተጠቀሱትን የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ዓለም አቀፍ ሕጎችን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ የተፈራረመች አገር መሆኗን የሚጠቁሙት አቶ ካሳሁን፤ «ይሕ እንደመሆኑም ሕጎች ተጥሰው ከተገኙ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ወስዶ ማሳየት ይገባል» ይላሉ፡፡

ይሑንና ረቂቅ ሕጎቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ እንሰራለን ከሚሉ ታላላቅ ተቋማት በኩል ሳይሆን በአሜሪካ መርቀቁ በራሱ ፍላጎቱ ሌላ ስለመሆኑ በቂ ፍንጭ የሚሰጥ ነው ሲሉ የሚተቹት በርካቶች ናቸው።

ምንም እንኳን ስቴት ሪፖርቲንግ (state reporting) የሚባል አቤቱታ አቀራረብ ቢኖርም የአሜሪካ አቤቱታ ግን ከመስፈርቱ ጀምሮ ሚዛናዊና እውነትን መሰረት ያደረገ እንዳልሆነም የሚያስረዱም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። በተለይም በአሸባሪው የህወሐት ቡድን በኩል የከፋ ሰብአዊ መብት ጥሰት መፈጸሙ እየታወቀ አሜሪካ ያረቀቀችው ረቂቅ ሕግ የኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ብቻ ትኩረቱን ያደረገና የሕግ ተጠያቂነት ለማስፈፀም የሚታትር መሆኑም ከጀርባ ስላለው ፍላጎት ግልፅ ጥቆማን የሚሰጥ እንደሆነ ይገልጻሉ።

የረቂቅ ሕጉ ይዘት ኢትዮጵያን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚጎዳና የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላገናዘበና አገሪቱ ለሰላም የዘረጋችውን እጅ ከግንዛቤ ያላስገባ» ሲሉ ይተቹታል። ረቂቅ ሕጉ በይዘት ደረጃ ሲታይ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ቀድሞውኑ በኢትዮጵያ መንግሥት የተመለሱ ስለመሆናቸውንም ያስገነዝባሉ።

ሰነዱ በኢትዮጵያ ካለው ሁኔታ አንጻር የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትን የተመለከተ ምርመራ እንዲካሄድ፣ ያልተገደበ የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭት እንዲኖርና አቅርቦቱ እንዳይስተጓጎል የሚጠይቅ መሆኑን በማንሳት፣ እዚህ ሶስቱም እንኳር ጉዳዮች ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ችግር እንደሌለበትና ጥያቄዎቹም እንደተመለሱም ይጠቁማሉ። ይህ እስከሆነም፣ «ጉዳዩ አሜሪካ እንደምትለው ስለ ሰብአዊ መብት አያያዝና አከባባር የሚጨነቅ ሳይሆን ፖለቲካዊ ፍላጎትን የተሸከመ ነው»ይላሉ።

በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን የሚያጋሩ ምሁራን፣ረቂቅ ሕጎቹ ለጊዜው ከመፅደቅ እንዲዘገዩ ተደርጓል ቢባልም ሰበብ ፈልጋ አሜሪካ አንድ ቀን እንደገና እንዳትመዘውና ሕግ አድርጋ እንዳታፀድቀው መደረግ ስላለበትም የሚሉት አላቸው። በተለይ በአሁን ወቅት የዳያስፖራው ማሕበረሰብ ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር መንግሥት ከፍተኛ ሃላፊነት እንዳለበት ይታመናል።

ከሕጎቹ አደገኛነታቸው አንፃር እንዳይፀድቁ ለማድረግ ምን ይደረግ በሚል ለተነሳላቸው ጥያቄ፣ የረቂቅ ሕጎቹ ኢትዮጵያን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚጎዱ በመሆናቸው ተቀባይነት እንዳያገኙ ከዚህም በላይ መቃወም እንደሚያስፈልግ አፅእኖት ሰጥተውታል። ይሕን የማድረግ ጊዜው ደግሞ ነገ ሳይሆን ዛሬ መሆን አለበት የሚለውም የጋራ ሃሳባቸው ሆኗል።

ሕጎቹ «ኢትዮጵያን ለማድቀቅ የተቀመሩ በመሆናቸው አምርረን እንድንቃወም ያደርጉናል። ይህ በኢትዮጵያ ላይ የተሰነዘረ አደገኛ ጥቃት ካላሰባሰበን፣ ሌላ ምንም ሊያሰባስበን አይችልም» የሚሉት የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን ግርማ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ተቃውሟቸውን እንዲያጠናክሩ ነው አፅእኖት የሰጡት።

ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል አገሪቱ ገጥሟት የነበረውን ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ጫና ለመቋቋም ዳያስፖራው ያስመለከተው ተጋድሎ፤ እነዚህ ረቂቅ ሕጎችም እንዳይፀድቁ ከምንጊዜውም በላይ በተቀናጀ በአንድነት ዘመቻ መንቀሳቀስ እንደሚገባ አስምረውበታል።

ምሁራን ረቂቅ ሕጉ እንዳይፀድቅ የማድረጊያው መንገድ በየት በኩል ነው የሚለውን ጥያቄም ሲመልሱ፤ እውነታውን ለማስገንዘብና ለማሳመን ጉዳዩ አሁን ባለበት የተቃውሞ ግለት ይበልጥ መቀጣጠል እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥና ማሻሻያዎች እንዲሁም እስረኞችን ከመፍታት ጀምሮ መንግሥት ለሰላም የዘረጋውን እጅ ማስገንዘበን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በማካሄድ ረቂቅ ሕጎቹ እንዲሰረዙ በማድረግ ረገድ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር መሆኑንም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ብልሃት የተሞላበት ዲፕሎማሲ መከተል እንዳለበት ያስገነዘቡት ምሁራኑ፤ «የምንፈለገው የእድገት ደረጃ እስክንደርስ ዓለም አቀፍ ግንኙነታችንና የዲፕሎማሲ ሥራችንን በእልህ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በእውቀት ላይ የተመረኮዘ መሆን መቻል አለበትም።» ነው ያሉት። በተለይም የሁለቱን አገራት ከመቶ አመት በላይ ያስቆጠረ ግንኙነት በሚያውክ መልኩ መሆን እንደሌለበትም ሳያስገነዝቡ አላለፉም።

የሕግ ባለሙያው አቶ ካሳሁን በበኩላቸው፤ መንግሥትም ቢሆን እውነታነት አላቸው የሚባሉ ጥሰቶች ከተገኙም ፈጣን የእርምት መውሰድና ተጠያቂ መሆን ያለባቸው አካላት ካሉም እርምጃን መውሰድ እንዳለበት ነው ያሰመሩበት።

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አቶ እንዳለ ንጉሴ በበኩላቸው ፣ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ ረቂቅ ሕጉ ላይ ትግሉንና ተቃውሞውን መቀጠል እንዳለበትና ይህን ረቂቅ ሕግ የሚያዘጋጅ አካል ከኢትዮጵያውያን ላይ እጁን እንዲያነሳ አበክሮ መታገል እንደሚጠይቅ አሳስበዋል።

መንግሥት በዲፕሎማቶቹ በኩል ለመላው አፍሪካውያንና ወዳጅ አገራት አሜሪካ አፍሪካን በእጅ አዙር ቅኝ ለመግዛት የምታደርገውን እንቅስቃሴና የዚህን ረቂቅ ሕግ አደገኝነት ግልፅ በማድረግ ትግል ማድረግ እንደሚገባ ነው ያመላከቱት። አይሆንምን ትቶ ይሆናልን እያሰቡ ቅድመ ስራዎችን መስራት እንደሚያስፈልግም ነው ያሰመሩበት።

መገናኛ ብዙሃንም በዚህ ረቂቅ ሕጉ ዙሪያ ለማሕበረሰቡ በቂ ግንዛቤ ከመስጠትም በላይ ይህ ሕግ እስከ መጨረሻው ድረስ ተቀባይነት እንዳይኖረውና ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲደረግ በትኩረት መስራት እንዳለባቸው ሳያስገነዝቡ አላለፉም። ሕጎቹ እንዲዘገዩ ሳይሆን እንዲቀሩ ማድረግ የግድ ነው የሚለውም የአስተያየት ሰጪዎች የጋራ እሳቤ ሆኗል። የፌደራል መንግሥትም በአገርም ሆነ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ የኢትዮጵያውያን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች ሕጎቹ እንዲሰረዙ የጀመሩትን ጥረት እንዲያስቀጥሉ ሲል ጥሪ ማቅረቡ የሚታወስ ነው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# 40 ዓመታትን በነፍስ ማስቀጠል ተግባር

## ‹‹እኔ እያለሁ አንድም እናት ቤት አትወልድም››

ሲስተር እታለማሁ ገብረዮሐንስ

**ሰላማዊት ውቤ**

ሴቶች ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ሕይወት የማስቀጠል ፀጋ የተጎናፀፉ ድንቅ ፍጡሮች ናቸው። ነገ ልምላሜ ሕይወት ያለው ተስፋ የሚሰጥ፣ ዓለምን የሚያገለግል፣ ለሕዝብ የሚቆም "ሰው" የሚባል፤ በጣም ክቡር የሆነ ፍጡር በሴቶች አማካኝነት ነው ዓለምን የሚቀላቀላት። በመሆኑም የጤና ባለሙያዎች እነዚህ እናቶች በወሊድ ወቅት በደም መፍሰስ፣ በፌስቱላና በሌሎች የጤና ችግሮች ምክንያት ሕይወታቸውን እንዳያጡ፤ ፅንሱም በአጭር እንዳይቀር እጅግ ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋሉ።

የዛሬ እንግዳችን ሲስተር እታለማሁ ገብረዮሐንስ ይህንኑ የተቀደሰ ተግባር ሲያከናውኑ ከቆዩ የጤና ባለሙያዎች አንዷ ናቸው። በሙያቸው አዋላጅ ናቸው። ከባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ጀምሮ ከሥራ ገበታቸው በጡረታ ቢገለሉም 40 ዓመታትን ሕይወትን በሚያስቀጥል ሙያ አገልግለዋል። ከአራት አሥርቱ ዓመታት የሥራ ዘመናቸው ስድስት ዓመታቱን በሻኪሶ ሆስፒታል ነው ያገለገሉት። ሁለቱን ዓመታት ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሰርተዋል። ቀሪዎቹን 32 ዓመታት በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል በመሥራት ነው ሙያዊ አገልግሎታቸውን ያጠናቀቁት። ወደ እናቶች የማዋለድ ሕክምና ሙያ የገቡት በ20 ዓመታቸው ሙያዊ ስልጠና በመውሰድ ነበር። በሙያው ያላቸው የትምህርት ዝግጅት ከታች ከመለስተኛ ጤና ረዳት ይጀምራል። ከመለስተኛ ጤና ረዳት ወደ ጤና ረዳት ለማደግ የሚያስችል ትምህርት ተከታትለውም የትምህርት ደረጃቸውን አሻሽለዋል። የማዋለድ ሙያቸውን ስለሚወዱት በሙያው ከዲፕሎማ እስከ ዲግሪ ለመዝለቅ በቅተዋል።

«ሙያዬ በየጊዜው ባሻሻልኩት ትምህርት መታገዙ የ40 ዓመት አገልግሎቴን ስኬታማ አድርጎልኛል» የሚሉት ሲስተር እታለማሁ በዚህ ጊዜ ውስጥ ካዋለዷቸው በሺህ የሚቆጠሩ እናቶች መካከል የአንዲትም እናት ሕይወት እንዳልጠፋባቸውም በኩራት ይናገራሉ። በተለይ 32ቱን ዓመታት እንዳገለገሉበት የጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል ብዙ ስፔሻሊስቶች ስላሉና የተለያዩ የትድግና እርብርቦች ስለሚደረጉ የእናቶች ሞት ብዙም እንዳልነበረ ይገልፃሉ። በሆስፒታሉ ባለሙያ ሲያዋልዳት በዓመት አንድ እናት ከሞተች ሰራተኛው በሙሉ ከቤተሰብ ባልተናነሰ ሁኔታ ከፍተኛ ሀዘን ውስጥ ይወድቅ እንደነበርም ያወሳሉ። «በዓመት አንድ እናት የምትሞትብን ከአቅም በላይ ስለሚሆንብንና ከአምላክ የመጣን ሞት መከላከል ስለማንችል ነበር» ሲሉም ያብራራሉ።

«እጅግ ያሳዘነኝ እና አንድ ጊዜ የገጠመኝ ከውርጃ ጋር ተያይዞ ነበር» የሚሉት ሲስተር እታለማሁ እንዳከሉልን ሚቿ ውርጃውን እቤት ውስጥ ሞክራ ነበር ወደ ሆስፒታሉ የመጣችው። ስትመጣ እጅግ ብዙ ደም ይፈሳት ነበር። ደም ብዙ ወሰደች። ሕይወቷን ከሞት ለመታደግ ብዙ ርብርቦች የታከሉበት ሙከራ ተደረገላት። ስፔሻሊስት ሐኪሞችም ያለ የሌለ አቅማቸውን አሟጠው ጨረሱ። «ሆኖም ልናተርፋት አልቻልንም። በዚህች ሀገሯም ቤተሰቧም ብዙ በሚጠብቅባት ወጣት እናት ሞት ምክንያት በጣም ያለቀስኩበትና ያዘንኩበት ጊዜ አጋጥሞኝ አያውቅም። እኔ ብቻ ሳልሆን ሌሎች ሠራተኞችም በዚህ የተነሳ በሆስፒታሉ ውለን ምግብ ሳንቀምስ ነው ያደርነው» ሲሉም ባለሙያው በተገልጋዩ ጉዳት የሚሰማውን ጥልቅ ሀዘን ገልፀውልናል።

ሲስተር እታለማሁ በተለይ ከደም መፍሰስ ጋር ተያይዞ የእናቶችን ሕይወት ለመታደግ በሆስፒታሉ ያለውን ተሞክሮ አስመልክተው እንዳከሉልን ሆስፒታሉ በወሊድ ጊዜ በሚገጥማቸው ከፍተኛ የደም መፍሰስ ምክንያት የሚሞቱ እናቶችን ሕይወት ለመታደግ ደም የሚያዘጋጅበት ጊዜ አለ። እንደ ዕድል ሆኖ ያኔ የጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል በቅርቡ ወደ ጤና ሚኒስትር ከሄደው ከደም ባንክ ጋር ጎረቤት ነበር። በመሆኑም አንዲት ወላድ እናት ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ከመግባቷ በፊት ወይም በወሊድ ወቅት ደም የሚፈሳት ከሆነ ደም የሚዘጋጅበት ሁኔታ አለ። በፊት በፊት ታዲያ ከዚህ ከደም ባንክ ከመጣ ወይም ሆስፒታሉ ካዘጋጀው ደም ይሰጣትና በኋላ ላይ ቤተሰቦች እንዲተኩ የሚደረግበት አሰራር ነበር።

እንደ ሲስተር እታለማሁ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በተለይም አሁን ላይ ግን እናቶችን ከሞት ለመታደግ ሲባል ይህ አሰራር ቀርቷል። ለየትኛዋም እናት ደም ቤተሰብ አይጠየቅም። ለእናቶች ደም በነፃ ነው የሚሰጠው። ደም ከደም ባንክ ይመጣል። በዚህ ላይ በበጎ ፈቃድ ተነሳስተው ደም የሚለግሱ የማሕበረሰብ ክፍሎች አሉ። በመሆኑም እንደ ሲስተሯ በየትኛውም የጤና ተቋም እናቶች በአብዛኛው ለሞት የሚዳረጉት በወሊድ ወቅት ከፍተኛ ደም ስለሚፈሳቸውና በፈሰሳቸው ደም ልክ ተተኪ ደም በማጣት በመሆኑ የአሁን እናቶች ዕድለኞች ናቸው።

ሲስተሯ አሁንና ቀድሞ በጤና ተቋማት የነበረውን ሁኔታ እያነፃፀሩ እንዳጫወቱን «የያኔ የአገልግሎቱ አቅርቦት በዚያው ዘመን ልክ ፍላጎት የተሟላ ነበር። አንቡላንስን ጨምሮ የሕክምና መሳሪያዎች ነበሩ። አብዛኞቹ አስፈላጊ ነገሮች ስለነበሩ እናቶች በቂ አገልግሎት ያገኙ ነበር። ሆኖም በሰው ኃይል በኩል የነበረው እንደ አሁኑ በበቂ ሁኔታ የተሟላ አልነበረም። በሕክምና ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማግኘቱም አስቸጋሪ ነበር። በአብዛኛው በተለይ በማዋለድ በኩል በልምድ ይሰራ የነበረበት ሁኔታ ጭምር ነበር። በመሆኑም ያኔ የሥራ ጫናው ይወድቅ የነበረው ባለሙያው ላይ ነው። በትንሽ ባለሙያ ብዙ አገልግሎት መስጠት ግድ ይል ነበር። ጥቂት ከማይባሉ ዓመታቶች ጀምሮ ግን እግዚአብሄር ይመስገን መንግስት በዘረጋው አሰራር ባለሙያም ከየትምህርት ተቋሙ እየተማረ እየወጣ ወደ ሕክምና ሙያው መግባት በመጀመሩ በቀደምቱ የሕክምና ባለሙያዎች ላይ የነበረው ጫና ሊቃለል ችሏል። እናቶችም ባለሙያው ከነበረበት የሥራ ጫና የተነሳ በመጠኑም ቢሆን ከሚዘገይ የጤና አገልግሎት መላቀቅ ችለዋል።»

ሲስተሯ ስለ ነፍስ ጡር ሴት የሚሰማቸውን ስሜት አስመልክተው «እርጉዝ እናት ሳይ ደስ ይለኛል። ልቤ ርህራሄ ይሰማዋል። ይሄ ስሜት የኔ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም እንደሆነ አስባለሁ። ምክንያቱም አንድም የሁላችንም አመጣጥ በዚህ መንገድ ነው። ሁለትም ከእግዚአብሄር በታች በፈቃዱ ሕይወትን ምታስቀጥል ብቸኛ መንገድ እንደሆነች እንረዳለን» ይላሉ።

ለዘጠኝ ረጅም ወራቶች ስትጨነቅ የነበረችበትን ሸክሟን ጨምሮ ከባዱን የምጥ ወቅት ጭንቋን መጋራትና መረዳት እንደሚገባ ይመክራሉ። ትዕግስተኝነትም በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆነም ያሰምሩበታል። በሰላም ለመገላገሏ በባለሙያ የሚሰጣት እያንዳንዱ አገልግሎት አስተዋጾ እንዳለውም ያሳስባሉ።

«እኔ እያለሁ አንድም እናት ቤት አትወልድም» የሚሉት ሲስተር እታለማሁ እናቶች ልጆቻቸውን መውለድ ያለባቸው በጤና ባለሙያዎች በመታገዝ በሆስፒታል ውስጥ መሆን እንደሚገባውም አበክረው ይመክራሉ። ሲስተሯ እንደሚናገሩት በጤና ተቋም መውለዳቸው የእናቶችንም ሆነ የህፃናትን ሞት በመቀነሱ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጾ አለው። ሆኖም በ40 ዓመት የማዋለድ አገልግሎታቸው እንደታዘቡት፣ በተለይ ቀደም ባሉት ዓመታት በሀገሪቱ የገጠር አካባቢዎች በአብዛኛው እናቶች ልጆቻቸውን በቤታቸው ውስጥ ነበር የሚወልዱት። ይህ ደግሞ የእናቶች ሞት ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል።

በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም እሳቸው ይሰሩበት በነበረው ሻኪሶ ሆስፒታል አካባቢ ያሉ የሻኪሶ ገጠር አካባቢ አንዳንድ እናቶች ምጣቸው ሲመጣ በፍጥነት ወደ ጫካ ሄደው በአስገራሚ ሁኔታ ልጆቻቸውን በጫካ ውስጥ የሚወልዱበት ሁኔታ ጭምር መኖሩን በወሬ ደረጃ ይሰሙ እንደነበርም ይጠቅሳሉ። በእርግጥ ወደ ጤና ተቋም እየመጡ የማዋለድ አገልግሎት ያገኙ የነበሩት እናቶች ከተማ ውስጥ የሚኖሩ እንደነበሩ እርሳቸውም ያስታውሳሉ። ልጆችን በቤት ውስጥ የመውለድ ሁኔታ በተለይ በገጠሩ የሀገሪቱ አካባቢ እንደ ፊቱ አይብዛ እንጂ አሁንም ሙሉ ለሙሉ አለመቀረፉንም ይናገራሉ። ዛሬም በሀገራችን የገጠሪቱ አካባቢዎች ልጆቻቸውን በቤታቸው ውስጥ የሚወልዱ እናቶች እንዳሉም አበክረው ይገልፃሉ። ይህንን ሁኔታ ለመቀየር በሕክምና አገልግሎት ዘመናቸው በተለይም ሻኪሶ በነበሩበት ጊዜ ወላድ እናቶች ወደ ጤና ተቋሙ ባይመጡም እሳቸውም ሆኑ ሌሎች ባልደረቦቻቸው እናቶቹ ወዳሉበት ገጠር አካባቢ እየሄዱ ቤት ለቤት ጭምር በመዝለቅ ለገጠር ወላድ እናቶች በጤና ተቋም እንዲወልዱ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሲሰጡ መቆየታቸውንም ይናገራሉ። በዚህም እናቶች ወደ ጤና ተቋም እየመጡ እስከ መውለድ የደረሰ የተወሰነ ለውጥ መታየት መቻሉንም ያስታውሳሉ።



ፎቶ፡ በሰላማዊት ውቤ

ሲስተር እታለማሁ ገብረዮሐንስ

«እኔ እያለሁ አንድም እናት ቤት አትወልድም» በሚል የግል መርህ የሚመሩት ሲስተር እታለማሁ በሥራ ዘመናቸው ከሚሰሩበት ተቋም አልፈው በሚኖሩበት አካባቢና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እናቶች ልጆቻቸውን በጤና ተቋማት ውስጥ በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ እንዲወልዱ ግንዛቤ ሲፈጥሩ መቆየታቸውንም አንዳንድ የቀድሞ የሥራ ባልደረቦቻቸው ነግረውናል። በተለይ የጤና ረዳት አፀደ ወልዴ እንደነገሩን ሲስተሯ ወላድ እናቶችን ከሞት ለመታደግ ከነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ መንገድ ላይ የሚያገኟቸውን ነፍሰ ጡሮች ሳይቀር እያስቆሙ ክትትል ማድረግና አለማድረጋቸውን ከመጠየቅ ጀምሮ ልጆቻቸውን በአቅራቢያቸው ባለ በጤና ተቋማት እንዲወልዱ ሳያሰልሱ ምክር ይሰጡ ሁሉ ነበር። ሲስተር እታለማሁ እንዳወጉን እሳቸውም በጾታቸው ሕይወት የማስቀጠል ፀጋ ከፈጣሪ የተሰጣቸው እንስት እንደመሆናቸው ሁለት ሴቶች እና አንድ ወንድ ልጅ ወልደዋል። ሁለቱን ልጆቻቸውን ቀደም ብለው ይሰሩበት በነበረው ሻኪሶ ሆስፒታል አንዱን ልጃቸውን የወለዱት ደግሞ ለ32 ዓመታት አገልግለው በቅርቡ በጡረታ በተሸኙበት ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ ነው።

ሲስተር እንዳወጉን በተለይ ለአዋላጅ ባለሙያ ሴቶች በሚሰሩበት ተቋም መውለድ ትልቅ ዕድል ነው። እንክብካቤው ለሌሎች ተገልጋይ እናቶች ከሚሰጠው አገልግሎት የተለየ ባይሆንም አገልጋይ የነበረችው በተራዋ ስትገለገል ማየቱና ዕድሉን ማግኘቷ በራሱ ከፍተኛ ደስታን ይሰጣል።

እኛም የሲስተር እታለማሁን የ40 ዓመታት ተሞክሮ ስንቋጭ ደስታ ለማግኘት ደስታውን ለዘለቄታው ለማጣጣም የጤና ባለሙያ ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ወላድ እናቶች በጤና ተቋማት ውስጥ መውለድ አለባቸው እንላለን። በተለይ በቅርቡ እንዲህ እንደ ሲስተር እታለማሁ ለረጅም ጊዜ እናቶችን ሲያገለግሉ የቆዩ የጤና ባለሙያዎች በጡረታ በተሸኙበት መድረክ ተገኝተው በሕክምናው ውስጥ ያለፉት ዶክተር ወዳጄነህ መህረነ እንዳደረጉት ንግግር እናቶች በወሊድ ጊዜ ከደም መፍሰስ እና ፌስቱላን ጨምሮ ሌሎች ለሞት የሚያበቁ ውስብስብ ችግሮች ይገጥሟቸዋል። እናቶች ብቻ ሳይሆኑ ልጆች ሲወለዱ በሚገጥሙ አደጋዎች ሊታመሙ፣ አካል ጉዳተኛ ሊሆኑ እንዲሁም ሊሞቱና ብዙ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። ከወሊድ ጋር በተያያዘ አያሌ ቁጥር ያላቸው እናቶች ይሞታሉ። ለምሳሌ፡- የጋንዲ ሆስፒታል ባለሙያዎች ከስድስት አሥርት ዓመታት በላይ ለነፍሰ ጡር እናቶች ከእርግዝና ወራት ጀምሮ በወሊድ ወቅት ከፍተኛ ተከታታይነት ያለው የሕክምና አገልግሎት በመስጠት በሰላም ልጆቻቸውን እንዲገላገሉ ሲያደርጉ የቆዩ ባለውለታዎች ናቸው። ሌሎች ነባርም ሆኑ አዳዲስ የጤና ተቋማት ባለሙያዎቹን አርአያቸው ሊያደርጓቸው ይገባል።

«የማሕፀን ፅንስ በምንማርበት ጊዜ ዶክተሮቹ መምህሮቻችን ታካሚዋ ለክትትል መጥታ ከክትትል በኋላ ከአልጋ ስትወርድ ጫማዋን እንድናቀርብላት ያደርጉን ነበር» ሲሉ የሕክምና ሙያ ትምህርት ተሞክሯቸውን የሚጠቅሱት ዶክተር ወዳጄነህ የአሁኖቹ የጤና ባለሙያዎች ከድሮዎቹ የጤና ባለሙያዎች ለተገልጋይ እናቶች ክብር መስጠትን ገንዘብ ሊያደርጉ እንደሚገባ ይመክራሉ። እንደ ዶክተር ወዳጄነህ ይህች ነፍሰ ጡር የመጨረሻ ምስኪን ደሃ ብትሆንና የተበጠሰ ነጠላ ጫማ ብታደርግም ክብርና ክብካቤ መስጠት ለባለሙያው ግድ እንደነበር ያስታውሳሉ። እግሯ ላይ እብጠት መኖሩንና አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚደረገውም እጅግ ከፍተኛ አክብሮትና ጥንቃቄ የሞላበት እንደነበርነም ያወሳሉ።

ዶክተሩ እንደሚሉት እንደ እርጉዝ እናት የሚያምር ፍጡር የለም። ምክንያቱም ፍሬ እንደሚያፈራ እንደ ጎመራ ዛፍ ትመስላለችና ነው። እርጉዝ እናት ከሰማይ በታች እጅግ በጣም የሚከበር ፍጡርን የምትሰጥ ስለሆነች ይህችን እናት የሚያገለግል ባለሙያ ደግሞ እጅግ በጣም ሊወደድና ሊከበር የሚገባ ነው። ውለታው በገንዘብና በቁስ አይለካም ፤ አይገመትም። ቢሆንም ለረጅም ጊዜ አገልግሎቱ ዕውቅና እና ክብር ሊሰጠው፤ ሊበረታታም ይገባል።

**ማረሚያ**

ሚያዝያ 4 ቀን 2014 ኢ.ም በዚሁ ገጽ፣ "ሴቶች" አምድ ላይ ባሰፈርነው ጽሑፍ "የባከነው ጊዜ" ደራሲ መጠነወርቅ ሳሙኤል አባታቸው አቶ ሳሙኤል "የፅዳት ሰራተኛ" ተብለው የተገለፁት የ"ሂሳብ ሰራተኛ"፤ መጠነወርቅ ሳሙኤል "በፀሐፊነት የተቀጠሩት የንግድ ሥራ ኮሌጅ" ሳይሆን አሁን "የመንገድ ሥራ ባለስልጣን" ያኔ "የአውራ ጎዳና ባለስልጣን"፤ ዘጠነኛና 10ኛ ክፍል የተማሩትም "ብርሃነ ኢትዮጵያ ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት" ተብሎ እንዲስተካከል በጠየቁት መሰረት፤ ከይቅርታ ጋር በዚሁ መስተካከሉን እንገልፃለን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**በዛሬው አዲስ ዘመን ዱሮ ዓምዳችን በ1962 ሰ.ም የወጡ እትሞች አገላብጠን ብትናቧቸው መልካም ነው ያልናቸውን ዘገባዎች ይዘን ቀርበናል። ዘገባዎቹ አሁን ካለንበት የኑሮ ውድነትና ህገወጥ ግብይት ጋር የተያያዙ መሆናቸው ቀልባችንን ይበልጥ ስቦታል፤ አንዱ ዘገባ ከአንድ ግለሰብ የተላከ ጽሁፍ / የግል አስተያየት/ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ ዜናዎች ናቸው። መልካም ንባብ።**

ኃይለማርያም ወንድሙ

### በአገራችን የዘይት ተፈላጊነት

በአገራችን በየጊዜው በዘይቶች ላይ እየጨመረ የሚሔደው ዋጋ በጠቅላላ የኢትዮጵያን ሕዝብ በተክል ቅባት (ዘይት) እንዲጠቀም አስገድዶታል። እንደዚሁም በየዓመቱ የሚመላለሱቱ የጾም ወራቶች ማለት እንደ ዐቢይ ጾም ያሉት በእህል ዘይት መጠቀምን ይጠይቃሉ። የወደፊት የዘይት ሥራን ለማስፋፋት በአሠራሩም በአመራረቱም ረገድ ታላቅ ተስፋ ሊጣልበት ከሚችሉ አንዱ የገቢ ምንጭ ነው።

በእህል ዘይት በኩል ኢትዮጵያ ራስዋን የቻለች እንደምትሆን የተረጋገጠ ነው። በአገራችን ውስጥ የእህል ቅባት አወጣጥ ዘዴ ጎጃም በጣም የተመሰገነ ነው። ኢትዮጵያ በትንሹ የወይራ ዘይት ከውጭ አገር ታስመጣለች። እንደዚሁም ሆኖ ለተክል ቅባት (ዘይት) ከጊዜ ወደ ጊዜ ተፈላጊነቱ እየጨመረ በመሄዱ የእህል ዘይት ተፈላጊነት በማናቸውም ዘንድ ታውቋል።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምግብ የሚሆነውን ዘይት የሚያወጣው ከዘራቸውና ከአመረታቸው የእህል ዓይነቶች ነው። እንደዚህም የእህል ዓይነቶች ኑግ፤ ተልባና ሱፍ፤ ሰሊጥ ናቸው።

የቅባት እህላችን ኢትዮጵያ ወደ ውጭ እንደመላኩዋ መጠን፤ የነጠረ ዘይት ወደ ውጭ አትልክም። ምክንያቱም የአገራችን ገበሬዎች ለዘይት ማውጫ የሚሆኑትን የእህል ዓይነቶች በብዛት ስለሚያመርቱና ለገበያ ስለማያወጡ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል። በአገራችን ላይ አሁን በብዛት የሚገኙት የእርሻ መኪኖች ለዘይት መውጫ የሚሆኑትን የእህል ዓይነቶች በብዛት እንዲገኝ የሚያስችሉ ሆኗል። ምንም እንኳ ሲሴም የሚባለው ተክል በብዛት በአገራችን ላይ ባይገኝም፤ እንደነዚህ ያሉት ተክሎች፤ ጥሩ ዘይት የሚያስገኙ መሆናቸው ስለተገመተ፤ በብዛት ገበሬ እንዲዘራቸው ተደርጓል። የጥጥ ፍሬ ዘይት የሚያስገኝ ሆኖ ስለተገኘ ተንዳሆ ከሚገኘው የጥጥ አዝመራ በብዛት ለማግኘት ይችላል። የጐመን ዘር፤ የጉሎ ፍሬ የጥጥ ፍሬ ከሳር ዘሮች ተልባ በኢትዮጵያ ለዘይት ማውጫ የሚሆኑና በይበልጥ ጠቃሚ ሆነው የተገኙ ናቸው። ከእነዚህም ሌላ ፩ኛ. ሰናፍጭ ፪ኛ.ኑግ ፫ኛ.ለውዝ ፬ኛ.የዱባ ፍሬ ፭ኛ. ሱፍ ለዘይት ማውጫ በብዛት ይጠቀሙናል።

(መጋቢት 8 ቀን 1962 ዓ.ም )

### በጐጃም ጠቅላይ ግዛት በሀሰት የሚሠራባቸው 182 ሚዛኖች ተያዙ

ደብረ ማርቆስ፡(ኢ/ዜ/አ/) በጐጃም ጠቅላይ ግዛት በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኘው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ቅርንጫፍ መ/ቤት 182 ሚዛኖች ሀሰተኛ የሸቀጣ ሸቀጥ መመዘኛዎች እንዳይሠራባቸው ማድረጉን አቶ ገብረ ጻዲቅ ተክለ ጊዮርጊስ በሰጡት መግለጫ ለመረዳት ተችሏል።

የጠ/ግዛቱ ቅርንጫፍ መ/ቤት ረዳት አላፊ አቶ ገብረ ጻዲቅ ከዚሁ በማያያዝ በሰጡት መግለጫ ‹‹እነዚሁ ሐሰተኛ መመዘኛዎች የተያዙት ከደብረ ማርቆስ ከተማ ፺፯፤ ከቡሬ ከተማ ፲፬ ፤ ከባህር ዳር ከተማ ፳፰ ፤ ከዳንግላ ከተማ ፳፪ ፤ ከደጀን ከተማ ፳፩ መሆናቸውን ገልጠዋል።

ከነዚህ መመዘኛዎች መካከል የብረታ ብረት ብሎኖች፤ ጠጠሮች የባትሪ ድንጋዮችና እነዚህን የመሳሰሉ ሕገወጥ መሥፈሪያዎች ይገኙባቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ እውነተኛ ኪሎ ግራም መስለው በሞረድ የተሞረዱና እውነተኛ መስለው የሚታዩ ናቸው። በነዚሁ ሀሰተኛ በሆኑ መመዘኛዎች ሲጠቀሙ የተያዙትም ነጋዴዎች ጥቂቶቹ ፍርድ ቤት ቀርበው ሲቀጡ፤ ግማሾቹ በክስ ላይ የሚገኙ መሆኑን አመልክተዋል።

አቶ ገብረጻዲቅ ቀጥለውም ሲናገሩ አንዳንድ ዕውነትን የማይከተሉ የጨርቃ ጨርቅ ነጋዴዎች ልክነቱ ያልተረጋገጠ እንጨት ዘርግተው እውነተኛ ሜትር ነው በማለት በማታለል ለሕዝብ ሲሸጡ ተደርሶባቸው፤ ከዚሁ አድራጐታቸው እንዲቆጠቡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል ካሉ በኋላ፤ ነጋዴዎችን በሚገባ ለመቆጣጠር ተጨማሪ ሠራተኞችና በተለይ የፖሊስ ረዳት የሚያስፈልግ መሆኑን ገልጠዋል።

ከዚህም በማያያዝ፤ ሸማቹም ሕዝብ ቢሆን ሚዛን ማወቅና በተለይም ከንግድ ሚኒስቴር ሰዎች ጋር መተባበር ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ የኛው ብቻ ቁጥጥር አጥጋቢ አይሆንም፤ እንዲሁም የምግብ ዘይትና ቅባት የሚሸጡ ነጋዴዎች ትክክለኛውን ሊትር አዘጋጅተው መሸጥ እንደሚገባቸው አስረድተዋል።

ደላላዎችም እንደዚሁ ከባላገር የሚመጣውን ገበያተኛ እንዳያዋክቡ ቁጥጥር ሊደረግባቸው እንደሚገባ ጠቅሰው የጥጥ ሻጮችም ቢሆኑ ከወንዝ በሰበሰቡት ድንጋይ እንዳይገበያዩ አደራ ብለዋል።

(መጋቢት 4 ቀን 19 62 ዓ.ም )

### ጤፍን ከአሸዋ ቀላቅሎ ያቀረበው 50 ብር ተቀጣ

ደብረ ማርቆስ ፡(ኢ/ዜ/አ/) በጤፍ ውስጥ አሸዋ ቀላቅሎ ለመሸጥ ሲያስማማ የተያዘው ሽፈራው የስጋት 50 ብር መቀጫ እንዲከፍል ተፈረደበት።

ሽፈራው ገንዘቡን መክፈል ባይችል ግን በ፶ ቀን እሥራት እንዲቀጣ የደምበጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ባለፈው ሳምንት ውስጥ ባዋለው ችሎት በይኖበታል።

በሽፈራው የስጋት ላይ ይህ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠው፤ በሁለት ስልቻ ውስጥ አፈርና አሸዋ ቀላቅሎ ገበያ አውጥቶ ለመሸጥ ከተስማማ በኋላ ሲመዘን 170 ኪሎ ስለሆነ ያለመጠን ክብደት በማምጣቱ በጥርጣሬ ሲፈተሸ አፈርና አሸዋ ቀላቅሎ የተገኘበት መሆኑ ስለተደረሰበት ነው።

(መጋቢት 30 ቀን 1962 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ



### ሱዳን ብሔራዊ ስምምነትን ለማምጣት በሚል ያሰረቻቸውን ፖለቲከኞች ልትለቅ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ብሔራዊ መግባባትን ለማምጣት ሲባል የፖለቲካ እስረኞችን እንደሚለቅ የሱዳን ጦር አስታወቀ።

እርቅና መግባባትን ለማምጣት ሲባል እስረኞቹ በቀጣዮቹ ሁለትና ሶስት ቀናት ውስጥ እንደሚለቀቁ የጦሩ መሪና የአገሪቱ ሉዓላዊ የሽግግር ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሌ/ጄ አብዱል ፈታህ አል ቡርሃን አስታውቀዋል።

ቡርሃን የእስረኞቹን መለቀቅ በተመለከተ መግለጫ አውጥተዋል። በመግለጫው እስረኞቹን ለመልቀቅ የሚያስችሉ ሂደቶች መጀመራቸውን ገልጸዋል።

እስረኞቹን ከመልቀቅ ጋር በተያያዙ የህግና የፍትህ ጉዳዮች ላይ ከአገሪቱ ጠቅላይ አቃቤ ህግና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መምከራቸውንም ነው ቡርሃን የገለጹት።

የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ስምምነት ላይ የሚደርሱና የሚግባቡ ከሆነ ጦሩ ስልጣን ለመልቀቅና ለሲቪሊያን ለማስረከብ ዝግጁ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ጦሩ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አብደላ ሃምዶክ ይመራ የነበረውን የሲቪሊያን የሽግግር መንግስት አስወግዶ ስልጣኑን ከተቆጣጠረበት ካሳለፍነው ጥቅምት መጨረሻ ጀምሮ ሱዳን በነውጥ ላይ ነች።

ኢትዮጵያ፤ ሱዳን ያለባትን ውዝፍ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ እንድትከፍል ጠየቀች

ጦሩ እርምጃውን ገትቶ ስልጣኑን ለሲቪሊያን እንዲያስረክብ ደጋግመው የጠየቁ ሱዳናውያንም ወደ አደባባዮች በመውጣት ተቃውሟቸውን ገልጸዋል። ዓለም አቀፍ ተቋማትም የተለያዩ ጫናዎችን ሲያደርጉ ነበረ።

ሆኖም ሃምዶክን ወደ ስልጣን መልሶ የነበረው ጦሩ ዳግም በማባረር የራሱን የሽግግር ምክር ቤት አባላትን መምረጡና መሾሙ ይታወሳል።

ይህ ግን እምብዛም ከጫና አልታደገውም። ሁሉንም የሚያግባባ የሲቪል መንግስት ይመስረት የሚሉ ጫናዎችም በርትተዋል። ይህን ተከትሎም ይመስላል ለእርቅና ብሔራዊ መግባባት ዝግጁ ነን የሚሉት የጦሩ አመራሮች ያሰሯቸውን ፖለቲከኞች ለመልቀቅ የወሰኑት።

### ተመድ በ7 አገራት የተራቡ ህጻናትን ለመርዳት 100 ሚሊዮን ዶላር ለቀቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር



ህጻናቱ የተራቡት በአገሪቱ በተከሰቱት ጦርነቶች ምክንያት መሆኑን ተመድ ገልጿል።

ተመድ ጨምሮ በሰባት አገራት ለረሃብ የተጋለጡ ህጻናትን ለመርዳት 100 ሚሊዮን ዶላር መበጀቱን ገለጸ።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣው ሪፖርት መሰረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ናይጀሪያ፣ ኬንያ እና የመን የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህጻናት ለረሃብ ተጋልጠዋል።

በመሆኑን በነዚህ አገራት ለረሃብ የተጋለጡ ህጻናትን ለመታደግ 100 ሚሊዮን ዶላር በጀት መልቀቁን አስታውቋል።

የተመድ ማዕከላዊ አስቸኳይ ምላሽ ፈንድ እንዳሳወቀው በሰባቱ አገራት ባለው ጦርነት ምክንያት ለረሃብ የተጋለጡ ህጻናትን መታደግ ያስፈልጋል ብሏል።

ከጦርነቱ በተጨማሪም በሰባቱ አገራት በተከሰተ ድርቅ እና የኢኮኖሚ ምስቅልቅል ሚሊዮኖች ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን መመገብ እንዳልቻሉ ድርጅቱ በሪፖርቱ ገልጿል።

በሩሲያ እና ዩክሬን መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት ተጨማሪ ዜጎችን ለረሃብ እንደሚያጋልጥ ተመድ አስጠንቅቋል።

ሁለት ቢሊየን የዓለም ሕዝብ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ይኖራል- ተመድ

በየመን፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶማሊያ ያለው የረሃብ ሁኔታ ደረጃ አምስት ላይ የሚቀመጥ ነው ያለው ድርጅቱ በታሪክ አስከፊው የህጻናት ሞት ሳይከሰት ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ገልጿል።

በናይጀሪያ፣ ሱዳን፣ ኬንያ እና ኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ በአንጻራዊነት የተሻለ ቢሆንም በጊዜው ለረሃብ ለተጋለጡት ከወዲሁ ድጋፍ ካላደረግን ተመሳሳይ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል ተመድ አስታውቋል።

የዓለም የዳቦ ቅርጫት የሚባሉት ሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ውስጥ መሆናቸው የዓለምን ሲሶ ምግብ አቅርቦት አደጋ ላይ ጥሏል። ለረሃብ የሚጋለጡ ዜጎች ቁጥር መጨመሩንም ነው ድርጅቱ የገለጸው።

ተመድ ከአንድ ወር በፊት አሁን ላይ የረሃብ አደጋ ያጋጠማቸው ሰባቱን አገራት ጨምሮ ሌሎች አገራት ላሉ ተረጂዎች 43 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልገው መግለጹ ይታወሳል።

ይሁንና እንዲደጎም ካቀረበው የ43 ቢሊዮን ዶላር በጀት ውስጥ እስካሁን የተገኘው 6 ነጥብ 5 በመቶ ያህሉ ብቻ ከለጋሽ አገራት እና ድርጅቶች መገኘቱን አስታውቋል።

# ስፖርት

## ታላቁ ሩጫ በበቆጂ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረኮች ተሳትፎዋ ከሰበሰበቻቸው 58 ሜዳሊያዎች መካከል 18 የሚሆኑት (10 የወርቅ፣ 3 የብር እና 5 የነሃስ) ሜዳሊያዎች የተቆጠሩት የሯጮቹ መፍለቂያ ምድር በቆጂ ባፈራቻቸው አትሌቶች ነው። የስፖርታዊ ውድድሮች ሁሉ በኩር የሆነው ኦሊምፒክ እንደ ማሳያ ተነሳ እንጂ በቆጂ ያበቀለቻቸው በርካታ አትሌቶች የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ጨምሮ በተለያዩ ውድድሮች ላይ አገራቸውን አኩርተዋል። በማህጸነ ለምለሟ በቆጂ አሁንም በርካታ ታዳጊዎች ራሳቸውን ሊቀይሩ፣ አገራቸውን ሊያኮሩ በመሮጥ ላይ ይገኛሉ።

በቆጂን የአየር ሁኔታዋ፣ የቦታ አቀማመጧ እንዲሁም የአኗኗር ሁኔታው ተዳምሮ የአትሌቶች ምንጭ አድርገዋታል። ይህንን የተረዱና ለአትሌቲክስ ስፖርት ልዩ ፍቅር ያላቸው በርካቶች ይጎበኟታል፤ የውጭ አገራት አትሌቶችም ለልምምድ ብቅ ይሉባታል። የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎች ጥናት ከማድረጋቸው ባለፈ አትሌቶችን እና አሰልጣኞችን በተናጠል እንዲሁም ስለ በቆጂ የፊልም ባለሙያዎች ‹‹የሯጮቹ ምድር›› በሚል ርዕስ ዘጋቢ ፊልም ሰርተውለታል።

ይህም መልካም ዕድል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እንደ ቱሪዝም መስህብ ሳይቆጠር አገሪቷም በቆጂም ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቆይተዋል። አሁን ግን የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር አገርን በዓለም አቀፍ ደረጃ እያሳወቀ ካለው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በበቆጂ የሩጫ መርሃ ግብር መዘጋጀቱ ተሰምቷል።

በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን የምትገኘው በቆጂ፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድር ከፍ ብላ እንድትጠራ ያደረጉ ስመ ጥር ዓለም አቀፍ አትሌቶችን ያፈራች ከተማ መሆኗ አትሌትክስን ለማበረታታት እና ከተማዋን የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የበለጠ ተመራጭ ያደርጋታል። ይህን መልካም ዕድል ወደ ተሟላ አገር አቀፍ ስኬታማነት ለመቀየር እንዲረዳም በቆጂን ማዕከል ያደረገ አገር አቀፍ ፕሮግራም ለማካሔድ ዝግጅት በመደረግ ላይ እንደሚገኙም ተቋማቱ በጋራ ባወጡት መግለጫ አሳውቀዋል።

የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የተዘጋጀው ይህ የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር መርሃ ግብርም ‹‹ኢትዮጵያ ትሮጣለች›› በሚል መሪ ቃል በበቆጂ ከተማ ግንቦት 6 እና 7/2014 ዓ.ም ያካሂዳል። የዝግጅቱ ዋና ዓላማም የስፖርት ቱሪዝምን በተለይም የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ነው። የእውቅ ዓለም አቀፍ አትሌቶች መፍለቂያ የሆነችውን በቆጂ ከተማን ለማስተዋወቅ እና ከተማዋ እንድትነቃቃ ከማድረግ ባለፈም ለአዳጊ አትሌቶች ጥሩ የመወዳደሪያ መድረክ ለመፍጠር ያለመ መሆኑንም መግለጫው ጠቁሟል።



በመርሃ ግብሩ ላይም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሚከናወነው ታላቁ ሩጫ በበቆጂ ጎን ለጎን በአርሲ ሰንሰለታማ ተራሮች ላይ የተራራ መውጣት፣ የብስክሌት ውድድር እና በስመጥሯ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ የተሰየመው ‹‹ጥሩነሽ ዲባባ ሻሚፒዮንሺፕ›› ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊ የአትሌቲክስ ሰልጣኞች መካከል ውድድር ይደረጋል። በዚህም ላይ ታዋቂ አትሌቶች፣ የበቆጂ እና አካባቢው ነዋሪዎች እና ከተለያዩ አካባቢዎች የሚጓዙ ጤናቸውን ለመጠበቅ የሚሳተፉ ሯጮችን ጨምሮ 1ሺ200 ሰዎች ይሳተፋሉ የሚል ዕቅድ ተይዟል።

የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር በበኩሉ በቆጂና አካባቢውን የሚገልጽና የቱሪስት መስህብ የሚሆን መለያ ምልክት (land mark) የሚያስቀምጥ ይሆናል። በተጨማሪም ለኬንያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤት እያስመዘገቡ ያሉ የረጅም ርቀት አሸናፊዎችን በማፍራት የሚታወቀው ‹‹ኤልዶሬት›› ከተማ ከበቆጂ ጋር የከተሞች እህትማማችነትን ለመመስረት ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ታዋቂ ከሆኑት ውድድሮች አንዱ የሆነው ‹‹ኤልዶሬት ሲቲ ማራቶን›› የ2014 ታላቁ በቆጂ ሩጫ ላይ አሸናፊ የሚሆኑ አትሌቶች በሚቀጥለው ዙር በኤልዶሬት ከተማ ተገኝተው የውድድሩ ተጋባዥ ተወዳዳሪዎች እንዲሆኑም ከስምምነት ላይ ተደርሷል።

ይህ ዕድል በተለይ ታዳጊ አትሌቶች የተሻለ ተሞክሮ እንዲቀስሙ ከመርዳቱም በላይ በዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ላይ የመወዳደር ልምድ እንዲያካብቱ ይረዳል። በተጨማሪም የሁለቱን ከተሞች እህትማማችነትን በማጠናከር የቱሪዝም ፍሰትን እንደሚጨምር ይጠበቃልም ተብሏል በመግለጫው።

ሕብረት ባንክ
Hibret Bank

## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የሐራጅ ማስታወቂያ

ሕብረት ባንክ አ.ማ. በአቶቴ ሀዋሳ ቅርንጫፍ በኩል ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን ከዚህ በታች የተመለከተውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በግልጽ ሐራጅ (ጨረታ) አወዳድሮ ይሸጣል።

| የቅርንጫፍ ስም | የተበዳሪ ስም | የአስያዥ ስም | ቤቱ የሚገኝበት አድራሻና የቦታው ስፋት | የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር | የሐራጅ መነሻ ዋጋ በብር | ሐራጁ የሚካሄድበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አቶቴ አዋሳ | ዱጉና ዩቱራ ቱሙሉ | ቀጀልቱ ጋሊቶ አዶሌ | ሐዋሳ ከተማ፣ ታቦር ክ/ከተማ፣ ሂጣታ ቀበሌ፣ የቤቱ ስፋት 250 ካ.ሜ የሆነ ለመኖሪያነት የሚውል ቤት፤ | 7178 | 2,097,328.00 | ግንቦት 16 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ ከ4፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት |

**የሐራጅ ደንቦች**

1. ተጫራቾች የሐራጁን መነሻ ዋጋ አንድ አራተኛ በባንክ ክፍያ ማዘዣ (ሲ.ፒ.ኦ) ብቻ በማስያዝ መጫረት ይችላሉ።
2. አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ አጠቃልሎ ካልከፈለ ያስያዘው ገንዘብ ለባንኩ ገቢ ሆኖ ሐራጁ ይሰረዛል። በተጨማሪም ንብረቱ ድጋሚ ለሀራጅ ሲቀርብ ለሚታየው የዋጋ ልዩነት ይጠየቃል።
3. በሐራጅ ላይ መገኘት የሚችሉት ተጫራቾች ፣ ተበዳሪዎች እና አስያዦች ብቻ ናቸው።
4. የሐራጁ ሽያጩ የሚካሄደው የመያዣው ንብረት በሚገኝበት ቦታ ላይ ነው።
5. የተጫራቾች ምዝገባ ከሐራጁ መዝጊያ ሰዓት ሰላሳ ደቂቃ በፊት ይጠናቀቃል። በሐራጁ ሰላሳ (30) ደቂቃዎች የተጫራች ምዝገባ አይካሄድም።
6. ለሐራጅ የቀረበውን ንብረት ለመጎብኘት የሚፈልጉ ከአበዳሪው ቅርንጫፍ ጋር አስቀድሞ ቀጠሮ በመያዝ ከጨረታው ቀን ሶስት ቀናት አስቀድሞ መጎብኘት ይችላሉ።
7. የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሌሎች ገዥ እንዲከፍላቸው በህግ የተወሰኑ የታክስና ግብር የስም ማዛወሪያ ጭምር /የጨረታው አሸናፊ/ ገዥው ይከፍላል።
8. ባንኩ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
9. ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር ፣ 0462 12 51 75/7288 አቶቴ ሀዋሳ ቅርንጫፍ ወይም 011-5-57-37-72 /0114704103 ሕግ አገልግሎት መምሪያ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።

**ሕብረት ባንክ**

## INVITATION TO BID

**National Competitive Bid (Open Bid)**

**THE FDRE MINISTRY OF REVENUES (MOR)**

Procurement Reference number: MOR/ITG/UB/D/08/2014

1. The Ministry of Revenues invites sealed bids from eligible bidders for the supply and delivery of UPS Static **Bypass Switch and UPS Battery.**

| No. | Description of goods and Services | Unit | QTY | The amount of the Bid security |
|---|---|---|---|---|
| 1 | UPS SYMMETRA PX static Bypass switch 160KVA/160KW | pcs | 1 | Birr 10,000.00 (Ten Thousand) |
| 2 | UPS performance Battery unit | pcs | 216 | Birr 100,000.00 (One Hundred Thousand) |
| | The detailed Specification for each items attached in the bid document. | | | |

2. Bidding will be conducted in accordance with the open national tendering procedures contained in the Public Procurement Proclamation of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and is open to all bidders from eligible source countries.
3. A bidder shall be required to supply the sample of their respective offer, as a condition of the contract award.
4. A bidder shall be required to supply renewed Business Licenses - Registration Papers, Tax Payment Certification, and also some other authenticated documents stated in the bid document as a requirement of MOR.
5. A complete set of Bidding Documents in English Language may be purchased by interested Bidders at the address below upon payment of a non-refundable fee of Birr 100.00 in cash.
6. Bids must be delivered to the address below at or before 4:00 a.m. (local time) on May 6, 2022, and will be opened in the presence of the bidders' representatives who choose to attend at the Ministries Meeting hall Building/ Block B/ 3RD Floor Office NO. 301 at 4:30 a.m. (local time) on May 6, 2022, all bids must be accompanied by a bid security of Birr with the amount stated above in the table or with an equivalent amount in a freely convertible currency. Late bids shall be rejected.
7. The Ministry reserves the right to reject in part or all bids.
8. The Address referred above is:

**Ministry of Revenue, HQ**
**The Procurement Team**
**Block B 3RD Floor, Room No. 301**
**Contact Person, Dawit Tesfaye**
**Tel-011- 617-84-90 and Email- dawittztml9@gmail.com**
**Addis Ababa, Ethiopia**

**Ministry of Revenue**